# በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ባህልነክ ፅሁፎች መዘርዘር ከአጫጭር መግለጫ ጋር

(ከ1994-1995)

በ

ትዕግስት ከበደ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለአርትስ

ባችለር ድግሪ ማሟያ የቀረበ

ጥናታዊ ፅሁፍ

አማካሪ

ወ/ሮ ኩሪ ባይሳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

# ምስጋና

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተሰበረውን የህይወቴን ድልድይ እየጠገነ እዚህ ላደረሰኝ እግዚአብሄር ምስጋና ያንስብሀል እለዋለሁ፡፡ስራዬን በማረም እና በማስተካከል ከጎኔ ላልተለየችኝ አማካሪዬ ለመምህርት ኩሪ ባይሳም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

እንዲሁም ለዚህ ያበቁኝን ቤተሰቦቼን ፍቅርና ሰላም ሳይለያችሁ ኑሩልኝ እላለሁ፡፡ ነገር ግን ለውዱ እና ለልዩው ወንድሜ ታሪኩ አማረ ምስጋናዬን ቃላት ብቻቸውን አይገልጹለትም፡፡ በተጨማሪም ከጎኔ ሆነው ሲያበረታቱኝ ለነበሩት ጓደኞቼ ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

## ማውጫ

**ርእስ** **ገጽ**

**ምስጋና** ....................................................................................................i

**ምእራፍ አንድ**

**1.መግቢያ**

1.1 የጥናቱ ዳራ.........................................................................1
1.2 የጥናቱ አላማ.......................................................................1
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታዎች ..........................................................1
1.4 የጥናቱ ገደብ .......................................................................2
1.5 የአጠናኑ ዘዴና አደረጃጀት...............................................2

**ምእራፍ ሁለት**

**2. ክለሳ ድርሳን**

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.................................................. 3
2.2 መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር
2.2.1 የመዘርዝር ምንነት ..................................................................5
2.2.1.1 የመዘርዝር ጥቅም ..........................................6
2.2.2 የአጭር መግለጫ ምንነት...........................................6
2.2.2.1 የአጭር መግለጫ ጥቅም.....................................7

**ምእራፍ ሶስት**

**3.ከ1994 — 1995 ዓመተ ምህረት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ባህል ነክ ዜናዎችና መጣጥፎች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር**

3.1 በህትመት ቅደም ተከተል ................................................... 8
3.2 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከ1994 — 1995 ዓመተ ምህረት የወጡ ባህል ነክ ዜናዎችና መጣጥፎች ዝርዝር በደራሲዎች ስም ቅደም ተከተል ............................................................. 38

**ምእራፍ አራት**

ማጠቃለያ እና አስተያየት........................................................ 45
ዋቢ ጽሁፎች
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

## ምዕራፍ አንድ

### 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

አዲስ ዘመን ጋዜጣ በሀገር ውስጥ በአማረኛ ቋንቋ ከሚታተሙት እለታዊ ጋዜጦች ውስጥ አንዱ ነው:: ይህ ጋዜጣ እስከ መስከረም 7/1993 ዓ.ም ድረስ በሳምንት ስድስቱን ቀን ይኸውም ከሰኞ በስተቀር ይታተም ነበር:: ከዚህ ቀን በኋላ ግን ዕለተሰንበት በሚል ርዕስ እሁድ እሁድ የሚታተመውን ሳምንታዊ ጋዜጣ ጨምሮ ሰባቱን ቀናት የሚታተም ነው::

አዲስ ዘመን ጋዜጣ የተለያዩ ሀያ ሰባት የሚደርሱ ቋሚ አምዶች አሉ፡እነዚህ አምዶችም ትኩረታቸው የሃገሪቱን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን መቃኘት ነው::

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ትኩረትም ከጋዜጣው ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ በሆነው ባህል ነክ ዜናዎችና መጣጥፎች ላይ ነው ::

ለዚህ ጥናት አነሳሽ የሆነው ምክንያት በጋዜጣው ውስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ባህል ነክ በሆኑት ዙሪያ የተጠኑ ወይም የተሰሩ የመመረቂያ ፅሁፎች አለመኖራቸው ነው::

### 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አላማ በተጠቀሱት ሁለት አመታት ውስጥ በ ጋዜጣው ላይ የወጡትን ባህል ነክ ዜናዎችና መጣጥፎች መለየት፣ሰብስቦ እና አጫጭር መግለጫዎ ች ተሰጥቶባቸው በታሪክ ቅርስነት ማቆየት ነው::

### 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

1. ጋዜጦቹ የተፃፉበትን ዘመን ማህበረሰብ ባህላዊ ጉዳዮች ሲያነሱ የዚያን ማህበረሰብ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ ....... ሁኔታዎችን እንዲሁም በወቅቱ የሚደረ ጉ ታላላቅ ክንዋኔዎችን ያካትታሉ:: እነዚህን ሰብስቦ አጫጭር መግለጫዎች መስጠት በወቅቱ የነበረውን ማህበረሰብ ማጥናት ለሚፈልግ ቀጣይ ትውልድ ታሪካዊ ማስረጃነት አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል::

2. ለወደፊቱ በዚህ ርዕስ ጉዳይና በሌሎቹም ይህን በመሰሉ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች መነሻ ሊሆን ይችላል::

3. ፅሁፎችን በአንድነት ተሰብስበው ማግኘት ከጉልበትና ከጊዜ ቁጠባ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት በጋዜጣው ላይ የወጡት ባህል ነክ ፅሁፎች በቀን በወርና በአመት ከፋፍሎ ማስቀመጡ በፈለጉት ጊዜ የፈለጉትን ነገር በቀላሉ ለማግኘት ሊያግዝ ይችላል::

4. በተለያዩ ጊዜያት በጋዜጣው የወጡ ባህል ነክ ፅሁፎች ያነሱትን ጉዳይ፣ የተፃፉትን ጊዜና በማን እንደተፃፉ በትክክል ለማወቅ ያስችላል::

**1.4 የጥናቱ ገደብ**

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ትኩረት ከጋዜጣው ዋና ዋና አምዶች ስር ከሚቀርቡ ርዕስ ጉዳዮች አንዱ በሆነው ባህል ነክ ጉዳይ ላይ ይሆናል:: ሌሎች የተቀሩ አምዶችን አይጨምርም::

ከጊዜ አንፃር ጥናቱ ከ1994-1995 ዓ.ም ድረስ ባሉት ሁለት አመታት ውስጥ የወጡ ባህል ነክ ዜናዎችና መጣጥፎችን ያጠቃልላል::

**1.5 የአጠናኑ ዘዴ እና አደረጃጀት**

ጥናቱ በአብዛኛው የሚካሄደው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም (IES) ቤተመፃህፍት ውስጥ ነው:: ጋዜጦቹ በየሁለት ወሩ በአንድ ላይ ተጠርዘው ተቀምጠዋል:: በመሆኑም በተጠቀሱት አመታት የወጡትን የአዲስ ዘመን ጋዜጦች እያንዳንዳቸውን በነጠላ በማገላበጥ ባህል ነክ የሆኑ ዜናዎችና መጣጥፎች ይሰበሰበሉ:: ከዚያም ፅሁፎቹ እንደተ ገኙ የጋዜጦቹን ርዕስ፣ጋዜጦቹ የወጡበትን ወር፣ቀን፣ዓመተ ምህረት፣ ገፅ እንዲሁም አምድን በመፃፍ ይደራጃሉ:: በመጨረሻም ፅሁፎቹን በህትምት ቅደም ተከተላቸው መሰረት በመዘርዘር አጫጭር መግለጫ ይሰጥባቸዋል::

የዚህ ጥናት አደረጃጀት አራት ምዕራፎች አሉት:: የመጀሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ዳራ፣ አላማ፣ጠቀሜታ፣ ገደብ፣ የአጠናን ዘዴና አደረጃጀት የሚሉትን ያካትታል::

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ሲሆን ሁለት ክፍሎች አሉት:: የመጀመሪያው ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውንና ከዚህ በፊት የተደረጉ ጥናቶችን የሚዳስስ ነው:: ጥናቱ በፊት ከተደረጉ ጥናቶች በምንእንደሚለያይ እና እንደሚመሳሰል ጭምር የሚብራራበት ይሆናል:: ሁለተኛው የዚህ ምዕራፍ ክፍል የመዘርዘርና የአጫጭር መግለጫ ምንነት የሚገለፅበት ይሆናል::

ምዕራፍ ሶስት ደግሞ ከ1994-1995 ዓ.ም ድረስ በጋዜጣው የወጡ ባህል ነክ ዜናዎችና መጣጥፎችን በመዘርዘር አጫጭር መግለጫ ይሰጥባል:: በዚሁ ምዕራ ፍ ውስጥም የባህል ነክ ፅሁፎቹ በመዘርዘር በደራሲዎች ስም ፊደል ቅደም ተከተል ይቀርብበታል::

በምዕራፍ አራት ደግሞ ማጠቃለያን አስተያየት ይካተትበታል::

## ምዕራፍ ሁለት

## 2 . ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል ትምህርት ተመራቂ ተማሪዎች ብዙ ስራዎን ሰርተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ መፅሄቶች እና ጋዜጦች ወዘተ ላይ መዘርዘር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር የተሰጠባቸው ጥናቶች ናቸው፡፡

ይህ ጥናትም መዘርዘር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር በመሆኑ ከቀድሞዎቹ ስራዎች ጋር በቀጥታ ይዛመዳል፡፡ ጥናቱ በአዲስ ዘመን ጋዜጦች ላይ መሰራቱ ደግሞ ከሌሎቹ ጥናቶች ጋር ያገናኘዋል፡፡

በሌላ ርዕሥ የቀረበእና ከዚህ ጥናት ጋር ከሌሎች በተሸለ መልኩ ቀረቤታ ያላቸውን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

1. ጌታቸው ለገሰ (1974) - " አዲስ ዘመን ጋዜጣ በባህል መድረክ በባህልና ኪነጥበብ በማስተዋወቅ ያበረከተው ድርሻ (ከ1972-1974)

የዚህ ጥናት ትኩረት ባህልንእና የባህ ል ቅርሶች በጋዜጣው ላይ ያላቸውን ሽፋን የሚቃኝ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከዘህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ርዕስ ጉዳዩ ባህል ነክ መሆኑ እና በአንድ አይነት ጋዜጣ ላይ መሆኑ ነው፡፡ የሚለያይበት ደግሞ ይህ ጥናት ዜናና መጣጥፍ ላይ ያተኩራል፡፡ የጌታቸው ጥናት ግን ማንኛውም ፅሁፍ ላይ ያተኩራል፡፡ ሌላው ልዩነት ይህ ጥናት መዘርዘርና መግለጫ የሚሰጥበት ሲሆን ያቸው ጥናት ቅኝት ላይ ያተኩራል፡፡

2. ስሜነህ ታደሰ (1993) - " ከ1977-1982 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ስነፅሁፋዊ አስተያየቶች (ኒሶች) መዘርዘር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር " የሚል ሲሆን

የጥናቱ ትኩረት በተሰጠው ዓ.ም ውስጥ ያሉትን በጋዜጣው ላይ የወጡ ስነፅሁፋዊ አስተያየቶች (ሂሶች) መዘርዝርና አጫጭር መግለጫ መስጠት ነው፡፡ ሁለቱ ጥናቶች የሚያመሳስላቸው መዘርዝርና አጫጭር መግለጫ መስጠታቸው እና በአንድ አይነት ጋዜጣ ላይ መስራታቸው ነው፡፡ የሚለያዩት ደግሞ በርዕስ ጉዳይ ነው፡፡

3. ሀብታሙ ገዜ (1993) - ከመስከረም 1978 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 1988 ዓ.ም ድረስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጡ አጫጭር ልቦለዶች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር"

ይህ ጥናት አጫጭር ልቦለዶችን ከጋዜጣው ላይ በተጠቀሰው ዓመተ ምህረት ስብስቦ መዘርዘር እና አጫጭር መግለጫ መስጠት ላይ ያተኩራል። የዚህ ጥናትና የሀብታሙ ጥናት የሚመሳሰሉት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ መስራታቸው እና መዘረዘር ከአጫጭር መግለጫ ጋር መስጠታቸው ሲሆን በርዕሰ ጉዳይ ግን ይለያያሉ።

4. ታደለች ተስፋው (1987) - "ከ1955-1959 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ግጥሞች ናሙና መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎ ጋር "

ይህ ጥናት ግጥሞችን ሰብስቦ አጫጭር መግለጫ መስጠት ላይ ያተኩራል። ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ መሆኑ እ ና መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር የሚሰጥበት መሆኑ ነው። ልዩነታቸው ደግሞ የርዕስ ጉዳይ ነው።

5. ጌታነህ ፅጌ (1993) - " በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ቋንቋእና ትምህርት ነክ ፅሁፎች መዘርዝርና አጫጭር መግለጫዎቻቸው (1984-1987)

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በተጠቀሰው ዓመተ ምህረት የወጡ ቋንቋና ትምህርት ነክ ፅሁፎች ላይ መዘርዝርና አጫጭር መግለጫ መስጠት ላይ ነው። ሁለቱን ጥናት የሚያመሳስላቸው መዘርዝርና መግለጫ ሰጭ መሆኛና በተመሳሳይ ጋዜ ጣ ላይ መስራታቸው ነው። በርዕስ ጉዳይ ግን ይለያያሉ።

## 2.2 መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር

### 2.2.1 የመዘርዝር ምንነት

መዘርዝር በእንግሊዝኛው " Biblography" ለሚለው ቀጥተኛ ትርጉም ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ለዚህም ቀደምት ስራዎችን ማስተዋል ይቻላል በተጨማሪም እንደ ማስረጃ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> ....... መዘርዝር የመፃህፍት የመጣጥፎችና የልዩ ልዩ ሰነዶች ዝርዝር የሚይዝ ይሆናል፡፡ እንደተለመደው መዘርዝር መፃህፍት ወይም ዋቢ ነፃፍት ሲል መጣጥፎችንና ልዩ ልዩ ሰነዶችን ከመፃህፍት የቀጠራቸው ስለሚያስመስል መዘርዝር ቢባል ሳይሻል ይቀራል?(ፈቃደ አዘዘ፣ 1982 ፣ገፅ 15)

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ መዘርዝር / Biblography / በተለያዩ የእንግሊዝኛ መፃህፍት ውስጥ የተሰጡት ትርጉሞች እንደሚከተለው እናያቸዋለን፡፡

> መዘርዝር " Biblography" በመፅሀፍ የውጭ አካል ላይ የሚገኙትን የደራሲ ስም ፤ የመፅሀፍ ርዕስ ፤ የህትመት ዘመን፤ ያሳታሚ ድርጅት፣ ወዘተ ስርዓት ባለው መንገድ ጠብቆ የመጣ ላይ ጥበብ ነው፡፡[1] ( A.L.A Glossary of library term 1971, p-11)

ይህ ማስረጃ የሚሆነው መዘርዝር ጥበባዊ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም የሚመዘገቡት ወይም የሚዘረዘሩት ነገሮች የተፃፉበትና የታተሙት ለማን? የቀረቡበት ርዕስ በምን ? የታተሙት ደግሞ መቼ? እንዳሆነ ስማቸውንና ዘመናቸውን ስርአታዊ በሆነ መንገድ ይመዘግባል፡፡

በ " መዘርዝር " ስራ ውስጥ የሚቀርቡ ነገሮች የጋራ ባህሪ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህም ማለት የሚዘረዘሩት በአንድ ነገር ጉዳይ ላይ የቀረበ፣ በአንድ ጋዜጣ ላይ ወይም ሰነድ ወይም መፅሀፍ... ውስጥ ታትመው የሚገኙ ወይም ደግሞ አንድ ደራሲ የደረሰባቸው እንደሆነ ነው፡፡ እነዚህም የጋራ ባህሪ ያላቸው ስራዎች ተመዝግበው የቀረቡበት ስራ "መዘርዝር " ይባላል፡፡ እንደ ማስረጃም የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> በመካከላቸው የጋራ ባህሪ ያላቸው ለምሳሌ ደራሲያቸው አንድ የሆነ ታዛዥነታቸው ለአንድ ጉዳይ የሆኑ፣ አንድ ቦታ ላይ የታተሙ ወይም በአንድ ላይ ተሰብስበው ለሌላ የደራሲ ስራ

ተጨማሪ ምንባብ ወይም እንደመረጃነት የተቀመጡ
ስራዎች ወይም ዶክመንቶች ዝርዝር መዘርዝር ይባላል፡፡[2]
(The ALA Glossary of library and Information Science 1963,p-21)

የመዘርዝር አይነቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከልም "General bibliography", "Enumerative bibliography or descriptive bibliography" , "bibliography of bibliography" እና "Annotated bibliography" የሚባሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ይህ ጥናት የሚቀርበው Annotated bibliography (መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር) ነው፡፡

### 2.2.1.1 የመዘርዝር ጥቅም

መዘርዝር አንድ ፅሁፍ በማን ተፃፈ? የት ተፃፈ? የት ታተመ? ለስንተኛ ጊዜ ታተመ? ምን ያህል የገፅ ብዛት አለው? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚገለግል ነው ይህ ደግሞ አንባብያን ስለ አንድ ፅሁፍ መረጃ ለማግኘት የሚያባክኑትን ጉልበትና ጊዜን ይቆጥባል፡፡

በተለያዩ ሰዎችና ጊዜያት የተሰሩ ስራዎች ስርዓት ባለው መልኩ ተደራጅተው ከተቀመጡ ከትውልድ ትወልድ በተቀላሉ ሊተላፉ እና ቀጣይ መረጃ ፈላጊን ለመርዳት ያገለግላል በሌላ አገላለፅ የፅሁፎችን ርዕስ፣የደራሲ ስም፣ የታተሙበት፣ ዘመን ወዘተ ተመዝግቦ ለቤተ መፃህፍት ተጠቃሚዎ መቅረብ ተገልጋዮች አስተማማኝነት ያለው መረጃ በቀላሉ እንዲገኙ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

መዘርዘር ስለ አንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ ለሚፈልግ
ተመራማሪ ለምርምሩ የመነሻ ነጥብ ሆኖ ሊያገለግለው ይችላል፡፡
መዘርዝር በአንድ በታተመ ሰነድ ውስጥ የተኛው ዕውቀት
በቅርበት ይገኛል የሚለውን ብቻ ሳይሆን በፊት የሚያውቀውንና
ወደፊት የሚታወቀውን ይጠቁመዋል፡፡ [3]( colliers encyclopedia vol 4 1970.141)

### 2.2.2 የአጭር መግለጫ ምንነት

አጭር መግለጫ የአንድን ፅሁፍ የትኩረት አቅጣጫ ወይም ይዘት ለአንባብያኑ ማብራሪያ ወይም ገለፃ ለመስጠት ሲባል ይፃፋል፡፡ይህም በገለፃ መል የሚቀረብ ነው፡፡ ለዚህም እንደማስረጃ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡ አጭር መግለጫ ለአንድ ለተወሰነ

ጉዳይ የተሰጠ አጥር ምጥን ያለ ገለፃ ነው፡፡ [4]( Encyclopedia of library & information science, vol2,1968, p-425)

> አጭር መግለጫ ፅሁፍን የሚያብራራ፣ የሚገልፅ ወይም ይዘቱን የሚገመግም ማስታወሻ መሰል ፅሁፍ ነው፡፡ በተለይ በመፅሀፍት ዝርዝር ለመዘርዘር ምንባብ ወይም በቤተመፃህፍት ላሉ የመፅሀፍት ዝርዝር እንደመግቢያ የሚሰጥ ማስታወሻ ነው፡፡ [5](ALA glossary of library term 1972,p-5)

### 2.2.2.1 የአጭር መግለጫ ጥቅም

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው መዘርዝር የራ ሱ የሆነ ጠቀሜታ እን ዳለው ሁሉ አጭር መግለጫም የራሱ የሆነ ጥቅም አለው፡፡ የአጭር መግለጫ ዋነኛ ጠቀሜታ አንባቢ ወይም ተመራማሪ ጊዜና ጉልበት በማያባክን መልኩ የአንድን የፅሁፍ ስራ አጠቃላይ ምንነትእና ይዘት ም ን እንደሚመ ስል እንዲያውቅ የሚያደርግ ነው ፡፡ በአጠቃላይ ከመዘርዝር እና ከአጫጭር መግለጫ ምንነት አኳያ መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር ( Annotation bibliography ) ማለት የመፅሀፎች፤ የሰነዶች፤ የጋዜጣዎች የፈጠራ ስራዎች ወዘተ ዝርዝር ከአጫጭር ገለፃዎች ጋር የሚቀርቡበት የመዘርዝር አይነት ነው፡፡

መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር የሚባለው የመዘርዝር አይነት ከሌሎች የመዘርዝር አይነቶች የሚለይበትን ባህርያት በተመለከተ ደግሞ Enciclopidia of liberary and information science '... የአጫጭር መግለጫዎች መዘርዝር ሂስ ከመስጠት የተቆጠበ ነው"፡፡[6] በማለት ለግለፅ አስቀምጦታል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

### 3. ከ1994 -1995 ዓመተ ምህረት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ባህል ነክ ዜናዎችን መጣጥፎች መዘርዘር ከአጫጭር መግለጫ ጋር

#### 3.1 በህትመት ቅደም ተከተል

ኢዜአ፡- "በበዓሉ ዋዜማ ሳምንት ከ301 ሚሊዮን ብር በላይ ከባንክ ወጥቷል።''መስከረም 1/1994 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 1፣ ገጽ-1

ለበዓል ብዙ ወጭ መኖሩ የተለመደ መሆኑን ጠቅሷል።ነገር ግን ዘንድሮ በተለየ መልኩ የ1993 ዓ.ም አልቆ አዲስ አመት 1994 መግባቱን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በአንድ ሣምንት ብቻ 301 ሚሊዮን 665 ሺ 453 ብር መውጣቱን ገልጿል። ብሩም ለተለያዩ ሸቀጦች ገበያ ላይ መዋሉን አሳውቋል።

ስንዱ ሀይሌ፡ "ልጆች በአውደ አመት መስከረም 1/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 1፣ ገጽ 2

በኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ በዓል አከባበር ላይ የሴት ልጆችን አለባበስና የጭፈራ ሁኔታ ገልጻለች። ከዚህም ጋር አያይዛ የተለያዩ ነዋሪዎች የሰጧትን ሃሣብ ጠቅሳ የአዲስ ዘመን አከባበር በተለይ በሴት ልጆች ጭፈራ እንደሚከበር ዘግባለች።

ጌታቸው ሰናይ፡- "ህይወት ሀብትን መንከባከብ ለባህላዊ እሴት ጥበቃ'' መስከረም 1/1994 ዓ.ም፣አዳስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር1፣ገጽ 4

"የህይወት ሀብት " ማለት ልዩ ልዩ ዕፅዋትን እንስሳትን፣ ጥቃቅን ነፍሣትን፣ ህዋሳትን እንዲሁም ውስብስብ ትስስር ያለው ስነምህዳር

አጠቃላይ ሁኔታን የሚያካትት መሆኑን እና ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ገልጾ ይህን መጠበቅ ማለት መሆኑን ገልጿል፡፡

ታምሩ ወ/ሚካኤል "የባህል ማዕከሉ ለባህላዊ ሙዚቃ "መስከረም6/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣61 ኛ ዓመት፣ቁጥር 6፣ ገፅ 4

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል ጳጉሜ 3 ቀን 1993 ዓ.ም የአዲስ ዘመን 1994 ዓመተ ምህረት መግባትን ምክንያት በማድረግ በማዕከሉ አማካይነት ተማሪዎቹ የተለያዩ ብሔረሰቦችን የእንቁጣጣሽ ባህላዊ አለበበስ ለብሰው የተለያዩ ዝግጅቶችን ማቅረባቸውን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ይህን ማድረጋቸው ለባህል ሙዚቃዎች እና ታዋቂ ባህል አምባሳደሮችን ለማፍራት አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አስተያየት ሰጭዎችን አካቶ በሰፊው ዘግቧል፡፡

--------- "የጌዲኦ ብሄረሰብ ባህላዊ ቅኝት" መስከረም 6/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ቁጥር 6፣ ገጽ 6

ጌዲኦ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት አንዷ መሆኗን ጠቅሶ የአየር ሁኔታዋን፣ አመሰራረቷን፣ ባህላዊ አስተዳዳሯን፣ የሕዝቦቿን አመጣጥ በማካተት በሰፊው ዳስሷል፡፡

ኢዜአ፡- "በደቡብ ወሎ ዞን የባህል መድሀኒት አዋቂዎች ማህበር ተቋቋመ፡፡'' መስከረም 9/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣ ገጽ-5

በየመንደሩ ያሉ የባህል መድሀኒት አዋቂዎች ነን የሚሉ ግለሰቦች የስራ ፈቃድ ስለሌላቸው ህብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ያሳሰብትን የማህበሩ ሊቀመንበር ሼህ ሁሴን ሰይድን ጠቅሶ ማህበሩ ከትናንት ወዲያ መቋቋሙን ገልጿል፡፡

ታደለ ገድሌ፡- "የመስቀል በአልና አከባበር በሐድያ" መስከረም 13/1994 ዓ.ም አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 13 ፣ ገጽ-4

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የመስቀል በዓል ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ በሆነ መንገድ በየአመቱ መከበሩን ገልጿል፡፡ በሀድያ ዞን ባህልና ማስታወቂያ መምሪያ "የሀድያ ብሄረሰብ የመስቀል በአል አከባበር" በሚል ትዕግስት አሠማ፣ መለሰ አሺቦ፣ ደሣለኝ ደቦጭ እና ደሣለኝ ሀይለ መስቀል በአቀረቡት አጭር ጥናታዊ ጽሁፍ መሠረት እንዳደረገ ይገልጻል፡፡ ከዚህም በመነሣት መስቀል በየዓመቱ እንደሚከበር እና የአከባበሩን አጠቃላይ ሁኔታ በሰፊው ገልጿል፡፡

ሰለሞን ተስፋዬ፡- "የኢትዮ- ቻይና ግንኙነት ታሪካዊ እና ባህላዊ ትስስር እንዳለው ተመለከተ"፣መስከረም 22 1994ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 22፣ ገጽ-1

ኢትዮጵያና ቻይና በፖለቲካ በኢኮኖሚ በባህል መስኮች መልካም ግንኙነቶች አጠናክረው መቀጠላቸው በ2ቱ ሀገሮች ህዝቦች መካከል የጋራ ግንዛቤና ወዳጅነት እንዲጎለብት ያስቻለ መሆኑን ገልጿል፡፡ ህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ የተመሠረተችበትን 52ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ትናንት በብሄራዊ ትያትር በተከፈተው የፎቶ አልበም ኤግዚቢሽን ላይ ሁለቱ ሀገሮች የረዥም ዘመናት ታሪክና የባህል ትስስር እንዳላቸው ጠቅሷል፡፡ ይህም ርስ በርስ ያላቸውን ወዳጅነት የበለጠ እንደሚያጎለብተው ማስቻሉን ገልጿል፡፡

ዋኢማ፡- "ባህላዊ መድሀኒቶች በዘመናዊ መልኩ ተዘጋጅተው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተጠየቀ፡፡ መስከረም 23/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 23 ፣ገጽ 6

ከተፈጥሮ ዕፅዋት የሚቀመሙ ባህላዊ መድሀኒቶች ከዘመኑ የህክምና ቴክኖሎጂዎች ጋር ተዋህደው ለህብረተሰቡ ጠቀሜታ የሚውሉበት አሰራር እንዲመቻች ብሔራዊ ባህላዊ መድሃኒቶች ቀማሚዎችና ሀኪሞች ማህበር ጥሪ ማቅረቡን ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- “ሴቶች በባህል ተፅእኖ የልፋታቸው ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ተገለጸ፡፡” ጥቅምት 13/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 43፣ ገጽ 4

በባህል ተጽእኖ የተነሣ የልፋታቸው ተጠቃሚ ያልሆኑ ሴቶችን ከወንዶች እኩል የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ብዙ መስራት እንደሚጠይቅ የአማራ ክልል ሴቶች ጉዳይ ፅሕፈት ቤት ማስታወቁን ገልጿል፡፡ ጽ/ቤቱ ባካሄደው የሦስት ቀናት አውደ ርዕይ ሴቶችን የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንደሚጥሩ የክልሉን ሴቶች ጉዳይ ፅሕፈት ቤት የትምህርት እና የስልጠና ክፍል ሀላፊ ወ/ሮ ስመኝ ይመርን ጠቅሶ ገልጿል፡፡

ቤተልሔም ክፍሌ፡- “ባሕላዊ ተጽእኖዎች በኩለሜ ብሔረሰብ” ፣ህዳር 1/1994፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 61፣ ገጽ-10

በደቡብ ክልል በደራሼ ወረዳ በኩለሜ ብሄረሰብ አንድ ወንድ አንድን ሴት አጭቶ ካስቀመጠ በኂላ ሌላ ሴት የማግባት መብት አለው፡፡ ሴት ግን ለብዙ ጊዜ ጠብቃ ከሌላ ወንድ ጋር ጋብቻ ከፈጸመች በገንዘብ መቀጣት ይደርስበታል፡፡ በሌላ በኩል ከወንዱ ባልተናነሰ ግብርና ስራ ላይ ውላ ማታ ወንዱ ሲያርፍ እሷ ግን የቤት ስራዎችን መስራቷን እና የልጅ ማሣደግ ጫናም እሷ ላይ መሆኑን በመዘርዘር በሰፊው አስረድቷል፡፡ በዚህም ወ/ሮ ዘነበች ጨርቆሴ የደራሼ ልዩ ወረዳ ሴቶች ጉዳይ ኃላፊ ስለዚሁ ጉዳይ የሰጡት አስተያየትን ጠቅሶ ሴቶች በአስገድዶ መድፈር፣ በጠለፋና በጋብቻ ላይ ጋብቻን ጨምሮ የተለያዩ ተፅዕኖዎች የሚደርስበቸው መሆኑን ገልጿል፡፡ ችግሩን በማስመልከትም ፅሕፈት ቤታቸው ጥረት እያደረገ መሆኑን ማስረዳታቸውን ገልጿል፡፡

ዋኢማ፡- “ባሕላዊ የእፅዋት መድሃኒት ምርምር ተቋም ተቋቋመ፡፡ ” ህዳር 9/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 69፣ገጽ 6

በዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተደግፎ በባህላዊ መድሀኒቶች ላይጥልቅ ምርምር ለማድረግ የሚያችል "ደሸት" የተባለ ባህላዊ እፅዋት ምርምር ተቋም መቋቋሙን ገልጿል፡፡ የተቋሙ መመስረት የመድሀኒት እፅዋቶችን ለማራባት ለመመዝገብና በምርምር ለማበልፀግ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው የተቋሙ ባለቤት ሀኪም አበበች ሽፈራው የተናገሩትን ጠቅሶ ዘግቧል፡፡

ዋኢማ፡- "የቤተ ጉራጌ ባህል ማዕከል በብሄረሰቡ ተወላጆች ሊቋቋም ነው፡፡" ” ህዳር11/1994፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 71፣ ገጽ-6

በቤተ ጉራጌ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ለማድረግና የ17ቱን የቤተ ጉራጌ ህዝብ ህብረት ለማጠናከር የሚያስችል የቤተ ጉራጌን ባህል ማእከል ለማቋቋም መወሠናቸውን አንዳንድ ነዋሪዎች ጠቅሶ ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "በወጣቶች ባህልና ስፖርት ዙሪያ ውጤታማ ተግባር ለማከናወን ጥረት ይደረጋል፡፡" ህዳር 21/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 81፣ ገጽ- 1

የሀገሪቱን ወጣቶች የልማትና የዕድገት ሀይል ለማድረግ የብሄር ብሄረሰቦችን ባህል ለማዳበር ለመጠበቅ እና የስፖርት እንቅስቃሴን ለማጎልበት ሰፊ ጥረት እንደሚደረግ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ አስመልክቶ ዘግቧል፡፡

ዋኢማ፡- "አፋር ባህላዊ ቅርሶች ማሰባሰቢያ ማዕከልና ሙዚየም ሊገነባ ነው ተባለ፡፡" ኅዳር 28 1994 ፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 88፣ ገፅ 3

አፋር ባህላዊ ቅርሶች ማስታወቂያ ቢሮ ከ18 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ ወጪ የአፋር ባህላዊ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ማሳባሰቢያ

ማዕከልና ሙዚየም ለመገንባት ዝግጅት ማጠናቀቁን አስታውቋል፡፡ ማዕከሉም ጥንታዊና ታሪካዊ እንዲሁም ባህላዊ የሆኑ የአፋር ክልል ቅርሶችን ለማስቀመጥ እንደሚያገለግል በቢሮው የባህል መምሪያ ኃላፊ የሆኑትን አቶ መሀመድ አህመድ ከልገሌን ጠቅሶ ገልጿል፡፡

ታምሩ ወልደ ሚካኤል፡-_"ለባህል ስፖርት ብሄራዊ ዳኞች ስልጠና ተሰጠ፡፡" ህዳር 28/1994፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 88፣ ገጽ 9

የኢትዮጵያ ባህላዊ ስፖርት ፌዴሬሽን ለአስር ቀናት 14 የሁለተኛ ደረጃ ብሄራዊ ዳኞችን ማሰልጠኑን ገልጿል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ የኢትዮጵያ ባህላዊ ስፖርት ፌደሬሽን ኘሬዝዳንት የሆኑት አቶ ተመስገን አክሊሉ የገለጹትን ጠቁሞ ስልጠናው በአገር አቀፍ ደረጃ የሚታየውን የዳኝነት ችግር እንደሚያሶግድና የሀገራችን መለያ የሆነውን ባህላዊ ስፖርት ለማስተዋወቅ ዳኞች ሳይታክቱ መስራት እንዳለባቸው አሳስቧል፡፡

ዋኢማ፡- "የባህል ወረራን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡" ታህሳስ 1/1994 ዓ.ም፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 91፣ገጽ-7

የወጣቱን ስብዕና የሚሸረሽሩ የባህል ወረራዎችን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት በማካሄድ ላይ ይገኛል በማለት የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ማስታወቁን ገልጿል፡፡ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የባህል ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ የሆኑትን አቶ በቀለ አበባውን ጠቅሶ ጥናቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፊልሞች፣ መጽሄቶች፣ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ላይ ያተኮረ መሆኑን ገልጿል፡፡

ታምሩ ወልደሚካኤል ፡- "በገና ዕለት ባህላዊ ስፖርት ጨዋታዎች ተካሄዱ፡፡" ጥር 1/1994 ዓ.ም ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 121፣ ገጽ-10

የአዲስ አበባ ባህል ስፖርት ፌዴሬሽን ያዘጋጀውና በየዓመቱ የሚካሄደው የገናና ሌሎች ባህላዊ ስፖርቶች ውድድር በርካታ የስፖርት አፍቃሪዎች በተገኙበት መጠናቀቁን ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "የትዕይንት ጎንደር የስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ተጀመረ፡፡ " ጥር9/1994 ዓ.ም፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 126፣ ገጽ- 8

የትዕይንተ ጎንደር ፋሲለደስ ሁለገብ ስታዲየም በደማቅ ስነስርዓት መከፈቱን ገልጿል፡፡ ለ9 ቀናት በሚቆየው በዚሁ ፌስቲቫል ላይ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር የሚገኙ 143 ወረዳዎች የተለያዩ የስፖርት ውድድሮችን እንደሚያደርጉ የፌስቲቫል አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሹምዬ ወልደስላሴን ጠቅሶ ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "ትዕይንት ጎንደር የስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ተጠናቀቀ፡፡" ጥር 15/1994፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 126፣ ገጽ- 8

በጎንደር ከተማ ለሳምንታት ሲካሄድ የቆየው የትዕይንት ጎንደር አመታዊ የስፖርት ባህል ፌስቲቫል ባለፈው እሁድ በሴቶች መረብ ኳስ ውድድር እና በወንዶች እግር ኳስ ጨዋታ መጠናቀቁን ገልጿል፡፡

---------- " የአዲስ አለም ባህላዊና ታሪካዊ ጉዞ " ጥር 26/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፡ 61ኛ ዓመት፣ቁጥር 146፣ገፅ -4

ታሪካዊቷ የአዲስ አለም ርእሰ አድባራት ደብረ ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን 100ኛ ዓመት ጉዞዋ ከ1884- 1994 ያለው መሆኑና አዲስ አለም ከተማም ሆነች ቤተክርስቲያኗ የተመሰረቱት በአጼ ሚኒሊክ ልዩ ትዕዛዝ መሆኑን ገልፆ የተመሰረተው አዲስ አበባ ከተማ ከተመሰረተች 16 ዓመት ሳይሞላት በ 1893 ዓ.ም እንደሆነ አጠቃላይ ታሪኳን የተለያዩ ካህናትን ጠቅሶ አትቷል፡፡

---------“ የኢራን የባህል ሳምንት ” የካቲት 3/1994 ፣ አዲስ ዘመን ፣ 61ኛ ዓመት፣ ቀጥር 153፣ ገፅ -4

የኢራን እስላማዊ አብዮት የተመሰረተበትን 23ኛ አመት ምክንያት በማድረግ ለአንድ ሳምንት ያህል ለህዝብ ክፍት ሆኖ የቆየና የሀገሪቱን ባህል የሚያንጸባርቅ ኤግዚቢሽን በሩሲያ ሳይንስና የባህል ማዕከል በዚህ ሳምንት ሲካሄድ መቆየቱን ዘግቧል፡፡ ከጥር 27 እስከ ጥር 30 በቆየው የባህል ሳምንት ኤግዚቢሽን ላይ በኢራን ሰአሊያን እና በኪነጥበብ ባለሙያዎች የተሰሩ ስዕሎች የኪነ ህንፃ ውጤቶች፣ታሪካዊና ጥናታዊ የኢራንን ስልጣኔ የሚያመለክቱ የተፈጥሮ መስህቦችን የሚየሳዩ ፎቶግራፎች መታየታቸው ተዘግቧል፡፡

አማረች ተሰማ ፣ “ ባህልና ወግ ተረሳ እንዴ? ” ፣ የካቲት 10/1994 ፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ ቁጥር 160 ፣ ገፅ -4

እስከዛሬ አገራችንን ከሌሎች አገሮች ልቃ እንድትታይ ያደረጋት ባህልና ወጌ መሆኑን ጠቅሳ ዛሬ ዛሬ ግን ስልጣኔ ተብሎ የፈረንጆችን ባህል መያዛችንን ጠቅሳለች፡፡ እንደምሳሌም በታክሲ ውስጥና መንገድ ለመንገድ ከንፈር ለከንፈር የሚሳሳሙትን አመላክታለች፡፡ ባለፈው ሳምንት አንድ ታክሲ ውስጥ ሲሳሳሙ ያጋጠሟትን ወጣቶች ጠቅሳ ብዙ ስለሚወራለት ኤድስ አውቀው ይሆን? በማለት ማሰቧንና ለባህላችን መጥፋትም ማዘኗን ተርካለች፡፡

ኢዜአ “ በሰሜን ወሎ ባህላዊ ስፖርት ውድድር እየተካሄደ ነው፡፡ ” መጋቢት 1 ቀን 1994 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ቁጥር 181፣ ገፅ -11

በሰሜን ወሎ ዞን ስምንት ወረዳዎች መካከል ባለፈው ሰኞ የተጀመረ የባህላዊ ስፖርት ውድድር በዋድላ ወረዳ በኮን ከተማ በመካሄድ ላይ መሆኑን ተዘግቧል፡፡

ሰለሞን ጥዑመልሳን ፣ “ በአፋር ክልል በ18 ሚሊዮን ብር ወጪ የባህል ማዕከልና ሙዚየም ሊገነባ ነው፡፡ ” መጋቢት 6/ 1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 186፣ ገፅ -1

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በ18 ሚሊዮን ብር ወጪ የባህል ማዕከልና ሙዚየም ለመገንባት መዘጋጀቱን የክልሉ ባህል ማስታወቂያና ቱሪዝም ቢሮ ማስታወቁን ገልጿል፡፡

ኢዜአ ፣ “ በሐረር ከተማ የባህልና የንግድ ትርኢት ሊካሄድ ነው፡፡ ” መጋቢት 12/1994 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ቁጥር 192፣ ገፅ -6

በሐረር ከተማ ባህልና ንግድ ትርዒት ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አስተባባሪዎች ማስታወቃቸውን ገልጿል፡፡ ትርኢቱን ምክንያት በማድረግ የንግድ ኤግዚቢሽን የመላ ኢትዮጲያ የባህል ጉባኤና የምስራቅ ኢትዮጲያ ተጎራባች ክልሎች የስፖርት ውድድሮች እንደሚካሄድ ማስታወቃቸውንም አያይዞ ገልጿል፡፡

ዋኢማ ፣ “ ባህላዊ ወርቅ አምራቾችን ለማደራጀት የተደረገው ውጤት ሳይሳካ ቀረ፡፡ ” መጋቢት 17/1994 ፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ ቁጥር 197 ፣ ገፅ -12

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባህላዊ የወርቅ አምራቾች በማህበር በመደራጀት ዘመናዊ የአመራረት ዘዴን እንዲከተሉ ለማድረግ የተደረገው ሙከራ አጥጋቢ ውጤት ያለማስገኘቱን የክልሉ ውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ሃብት ቢሮ ማስታወቁን ገልጿል፡፡

ዋኢማ ፡- “ የዕደ ጥበብና ባህላዊ እቃዎች ለገበያ ስለሚውሉበት መንገድ እየተጠና ነው፡፡ ” ሚያዚያ 15/1994 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 225 ፣

ገፅ-2

በኢትዮጲያ በተለያዩ አካባቢዎች በባህላዊ መንገድ የሚመሰረቱ የዕደጥበብና የባህል እቃዎች ለውጥና ለሃገር ውስጥ ገበያ የሚውሉበት መንገድ በመጠናት ላይ መሆኑን የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች ድርጅት ማስታወቁን ገልጿል፡፡

ፀሀይ ለማ ፡- "ባህላዊ ጋብቻ በሶዶ ክስታኔ" ሚያዚያ 27 1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 237፣ ገፅ -4

የቤተ ጉራጌ አካባቢ በሆነው በሶዶ ክስታኔ ባህላዊ ጋብቻ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው እና በአሁኑ ወቅትም በገጠሩ የህብረተሰብ ክፍል እያንዳንዱ ስርዓትና ወግ ጠብቆ በስፋት የሚከናወን መሆኑን ገልፆ ስለባህላዊ ጋብቻም አብራርቷል፡፡

ኢዜአ ፡- "ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት 20 ሺህ ብር እና ባህላዊ ስእል ተበረከተ፡፡" ግንቦት 3 1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ ቁጥር 243፣ ገፅ 5

በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደር እና ባለቤታቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የፈረስ ጉግስ ጨዋታ የሚያሳይ ጥናታዊ ስዕልና የሃያ ሺህ ብር ስጦታ ማበርከታቸውን ገልጿል፡፡

ዋኢማ ፡- "በበርታ ብሄረሰብ አባላት በሚዘወተር ባህላዊ አደን የዱር እንስሳት ቁጥር ተመናመነ፡፡ " ግንቦት 4/1994 ዓ.ም፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ቁጥር 244፣ ገፅ -6

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በበርታ ብሄረሰብ አባላት ዘንድ በበጋ ወራት የሚዘወተረውን " ሲአዳ " ባህላዊ አደን መስፋፋት በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትን እንዲመናመኑና እነዲሰደዱ ማድረጉን የክልሉ ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ ማታወቁን ገልጿል፡፡ በቢሮው የቅርብ ጥናትና ጥበቃ ቡድን መሪ አቶ ገዛኸኝ

ይልማ ሰምራ የገለፁትን አስመልክቶ በተለይም በሸቆሌ ወረዳዎች አሰተባባሪነት የሚካሄደው አደን በዱር እንስሳቱ ህልውና ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን ዘግቧል፡፡

ኢዜአ ፡- " የጀርመን የባህል ተቋም 40ኛ ዓመቱን እንደሚያከብር ተመለከተ፡፡ "

ግንቦት 24 /1994 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን ፣ 61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 264 ፣ ገፅ 1

በኢትዮጵያ የጀርመን ባህል ተቋም የተመሰረተበት 40ኛ ዓመት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር በኢትዮጵያ የጀርመን ኢንባሲ ካውንስለር ማስታወቃቸውን ገልጿል፡፡

ጌትነት ገሰሰ፡- " የኢትዮጵያ - አረብ የባህል ስምምነት ከመጭው አርብ ጀምሮ ይከበራል፡፡ " ግንቦት 24/ 1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ቁጥር ፣ገፅ-1

የኢትዮ አረብ የባህል ሣምንት ከሚቀጥለው አርብ ጀምሮ በአዲስ አበባ እንደሚከበር ገልጿል፡፡ በዓሉ ለአትዮጵያና ለአረቡ ዓለም ግንኙነት ልዩ ትርጉም እንዳለው ጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም የባህል ሣምንቱ አዘጋጅ ኮሚቴ ትናንት የሰጠውን ጋዜጣ መግለጫ ጠቅሶ የኢትዮ አረብ ባህል ሣምንት ከግንቦት 30 ጀምሮ እስከ ሰኔ 6 ቀን እንደሚቆይ ገልጿል፡፡

ታደለ ገድሌ፡- " የባህል ግንባታ ከባህል ፖሊሲ አንጻር " ግንቦት 25/1994 ዓ.ም.፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 265፣ ገጽ- 4

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የባህል ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን ጠቅሷል፡፡ የባህል ፖሊሲ ሲባል ምንድን ነው? ፖሊሲው ምን ያህል ተግባራዊ ሆነ? ግንዛቤ አግኝቶ የብሔር ብሔረሰቦችን ባህልን በበለጠ ለማስተዋዋቅና ጐጂ ባህላዊ ልምዶችን ለማስቀረት ምን ዓይነት ጥረት ተደረገ? ፖሊሲው

ለባህል ግንባታ ለሠላም ማስፈንና ለዲሞክራሲ እድገት ያደረገው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? ባለፉት 11 ዓመታት ምን ያህል የባህል ግንባታ ተካሄደ? በሚሉና በሌሎች ጥያቄዎች ዙሪያ በባህል ሚኒስቴር የባህል ጉዳይ መምሪያ ሃላፊ አቶ በቀለ አበባውን ጠቅሶ አብራርቷል።

ኢዜአ ፡- " የጀርመን የባህል ኢንስቲትዩት የተመሰረተበት 40ኛ ዓመት ተከበረ። " ግንቦት 28/1994 ዓ.ም. ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 268 ፣ገጽ -1

"ጐቴ" በመባል የሚታወቀው የጀርመን ባህል ኢንስቲትዩት ኢትዮጲያ ውስጥ የተቋቋመበት 40ኛ ዓመት ትናንት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች መከበሩን ገልጿል። በዓሉ በአዲስ አበባ ውስጥ በአራት ኪሎ በሚኘው የኢንስቲትዩቱ አዳራሽ በተከበረበት ወቅት የሁለቱን ሀገሮች የቆየ ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነት የሚያንፀባርቅ ፎቶግራፍ የፖስተርና የበራሪ ጽሁፎች ኤግዚቢሽን ለሕዝብ ይፋ መሆኑንም ገልጿል።

አያሌው ንጉሤ፡- "በባህል ዘርፍ ላይ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርት ለመጀመር የሚያስችል ረቂቅ ጥናት ቀረበ። " ግንቦት 30 ቀን 1994 ዓ.ም.፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 270፣ገጽ- 3

የክልሎችን አቅም በሰለጠነ የሰው ሃይል ለማጠናከር በባህል ዘርፍ በዲኘሎማ ኘሮግራም መለስተኛ ባለሙያዎችን ለማፍራት ሥልጠና አስፈላጊ መሆኑን የሚጠቁም ጥናት ለውይይት መቅረቡን ገልጿል።

ታደለ ገድሌ፡- "የባህል ፖሊሲው ከሲኒማ ጥበብ አንጻር" ሰኔ 2/1994 ዓ.ም. ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 272፣ ገጽ- 4

አዲሱ የባህል ፖሊሲ በተለይ ለፊልም ጥበብ ትኩረት እንዳልሰጠና በዚህ ረገድ ለአገራችን የፊልም እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያደርግ የነበረው የኢትዮጵያ ፊልም ኮርፖሬሽን

መፍረሱ አግባብ እንዳልሆነ የፊልም ዳይሬክተሩ ተስፋዬ ስንቄ የሰጡትን አስተያየት አቅርቧል፡፡

መስፍን አብርሃ፡- “የባህል እንክብካቤ በትግራይ” ሰኔ 2/1994 ዓ.ም. ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት ፣ቁጥር 272 ፣ገጽ- 4

የባህል መገለጫዎች ባህላዊ ስፖርቶች ኪነጥበብ ሥነጥበብ ጽሁፍ የአኗኗር ስልት መሠረታዊ የሰው ልጆች መብት የዋጋ አጠቃቀምና ልማዳዊ ባህሎች የመሳሰሉት መሆናቸውን ገልጾ ከዚህ አኳያ በትግራይ ክልል ከ1988 ዓ.ም. ጀምሮ የትግራይ ማህበር መመስረቱን ጠቅሷል፡፡ የማህበሩ ከላይ የጠቀሰውን የባህል መገለጫዎች ለማጠናከር እየሠራ መሆኑንም አያይዞ ገልጿል፡፡

ቤተልሔም ክፍሌ:- “በባህላዊ ሕክምና ለተሰማሩ ሴት ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተጠቆመ፡፡” ሰኔ 7/1994 ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 277 ፣ገጽ -5

በባህላዊ የሕክምና አገልግሎት ሴተች የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ለሥራዎቻቸው እውቅና መስጠት በተጨማሪም ተገቢውን ድጋፍ የሚያነበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሴቶች ጉዳይ መምሪያ ሃላፊ ሴስተር ጽጌ የማነ አበራ ማስታወቃቸውን ገልጿል፡፡

ታደለ ገድሌ:- “ባህልና ወዳጅነትን የሚያጠናክር የስእል ኤግዚቢሽን” ሰኔ 9/1994 ዓ.ም. ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 279፣ ገጽ- 4

በሕንድ ብሔራዊ የኪነጥበብ አካዳሚ በላሊት ካለ አማካይነት የተዘጋጀና የአሁኑን ዘመን ሕይወት የሚያንፀባርቀው የሕንድ ስእል ኤግዚቢሽን በብሔራዊ ሙዚየም መከፈቱን ገልጿል፡፡ የባህል ኤግዚቢሽኑ ከህንድ ውጪ ሲቀርብ የመጀመሪያ ጊዜው መሆኑን ጠቅሶ በስእል ኤግዚቢሽኑ ላይ

የቀረቡት ስእሎች በታወቁ የሕንድ ሰዓልያን፣ በግራፊክና በቀለም ቅብ የተሣሉ መሆናቸውን አመልክቷል።

አያሌው ንጉሣ:- "የባህል ጉባኤው ለባህል እድገት" ሰኔ 16/1994 ዓ.ም. ፣አዲስ ዘመን 61ኛ፣ ዓመት ቁጥር 286፣ ገጽ- 4

ከግንቦት 28-30 ቀን 1994 በሐረር 3ኛው የባህል ጉባኤ መካሄዱን አስታውሶ ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡና በባህል ዘርፍ የተሠማሩ ባለሙያዎች በተገኙበት ጠቃሚ ውይይት መደረጉን ገልጿል። በርካታ ጥናታዊ ጽሁፎችም ቀርበው እንደተገለፀባቸውም ለኢትዮጵያውያን ወግና ባህል እንዲሁም ልማድ ጋሬጣ የሆኑ ክስተቶች በአንዳንድ ቦታዎች እየተፈጠሩ መሆናቸውን ጠቁሟል።

ኢዜአ:- "በወሊሶ የብሔር ብሔረሰቦችን ባህላዊ ሕይወታዊ ሃብቶች የሚያሳይ ኤግዚቢሽን ሊከፈት ነው።" ሰኔ 29/1994 ዓ.ም. ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 299፣ ገጽ 3

ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተውጣጡ ተማሪዎችን የሚያሳትፍ የባህላዊ ሕይወታዊ ሃብት ምንነትን እና ጠቀሜታን የሚያሣይ የሕይወታዊ ሃብት መንደር ኤግዚቢሽን ከሐምሌ 5 ቀን 1994 ዓ.ም. ጀምሮ በውለሶ ከተማ እንደሚከፈት አስታውቋል።

-------፣"የአላባ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ " ሐምሌ 7/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 307፣ ገፅ -4

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚኖሩት 45 ብሔረሰቦች ውስጥ የአላባ ብሔረሰብ አንዱ ነው። በዚህም ከሚከናወኑት የጋብቻ ዓይነቶች ውስጥ የውርስ ጋብቻ፣ በሁለቱ ወጣቶች ስምምነት የሚፈጸም የጠለፋ ጋብቻ እንዲሁም ሁለት ወንድማማቾች ከሁለት እህትማማቾች ጋር የሚፈጽሙት የጋብቻ ዓይነትና የሴቷ ፍላጎት የሚከበርበትን ጋብቻ "ኦጋ"

የሚሉት መሆናቸውን ጠቅሶ የእያንዳንዳቸውን የጋብቻ ዓይነቶች ባህላዊ ስርዓት አብራርቷል፡፡

ኢዜአ፣ "የክርስቲያንና የሙስሊሙን የሙዚቃ ባህል ለማስተዋወቅ የሚያስችል ሲንፖዚየም ሰሞኑን ይካሄዳል፡፡" ሐምሌ 14/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61 ዓመት፣ ቁጥር 314፣ ገጽ -5

የኢትዮጵያ ክርስቲያንና ሙስሊም ህብረተሰብ የሙዚቃ ባህልን የሚያስተዋውቅ ውይይት ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ አዲስ አበባ ውስጥ እንደሚካሄድ የጀርመን ካልቸራል ኢንስቲትዩት ማስታወቁን ገልጿል፡፡

ስንዱ ኃይሌ፣ "በባህላዊ ዘዴ የሚመረተው ወርቅ ኢኮኖሚያያዊ ጥቅም የሚሰጥበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑ ተገለጸ፡፡" ሐምሌ 27/1994 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ ዓመት፣ ቁጥር 327፣ ገጽ- 1

በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው በባህዊ መንገድ እየተመረተ በዓመት ወደ ውጪ የሚላከውንና የሚባክነውን ሶስት ሺህ ኪሎ ግራም መጠን ወርቅ በህጋዊ መንገድ ለአገር ኢኮኖሚ ጥቅም የሚሰጥበት መንገድ እየተመቻቸ መሆኑን ገልጿል፡፡ "የማእድን ሃብትና የኢንቨስትመንት እድል" በተሰኘው አውደ ርዕይ ላይ የማእድን ስራዎች መምሪያ ኃላፊ አቶ ጌታቸው ተስፋዬ የተናገሩትን ጠቅሶ አብራርቷል፡፡

ጌታቸው ሰናይ፣ "ባህላዊ ውበት - በወሊሶ" ሐምሌ 29 /1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61 ዓመት፣ ቁጥር 329፣ ገጽ -6

"በባህላዊ ህይወት ለአስተማማኝ ህልውና የህይወታዊ ሃብት መንደር" በተሰኘ ርዕስ የአካባቢ ተቆርቋሪዎ መድረክ የተዘጋጀ ኢግዚቢሽን እንደነበረ ገልጿል፡፡ በዚህም ተካፋይ የሆኑት በአገራአቸችን የሚገኙት ዘጠኙም ክልሎች መሆናቸውን ጠቅሶ የተለያዩ ወጣቶችን በተለያየ ብሄር ብሔረሰብ አልባሳት ተውበው ለዝግጅቱ ትልቅ ድምቀት እንደሰጡት ተሳታፊ የነበሩትን ጠይቆ የዝግጅቱን አስደሳችነት ገልጿል፡፡

ፈይሰል ኢብራሂም መሐመድ፣ "የሐረሪ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ" ነሐሴ 5/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61 ዓመት፣ ቁጥር 335፣ ገጽ -5

ከሐረሪ ብሔረሰብ በርካታ ድንቅ የባህል እሴቶች ውስጥ አንዱ ጋብቻ መሆኑን ጠቅሶ የዚህን የጋብቻ ሂደትና አፈጻጸም ባህላዊ ስርዓት በሰፊው አስፍሯል፡፡

----------------፣ "የቤንሻንጉል ጉሙዝ ባህላዊ ቅኝት" (ክፍል 1) መስከረም 5/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፣ ገጽ-4

በቤንሻንጉል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስደናቂና ለየት ያሉ የባህል እሴቶች መገኘቸውን ጠቅሷል፡፡ ከባህል እሴቶቹ ውስጥ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ግብረ ህንጻዎች፣ ገዳማትና የአምልኮ ቦታዎች፣ የተፈጥሮ መስህቦችና የብሔረሰቦችን የጋብቻ አለባበስና የግርዛት ስነስርዓት የሚያንጸባርቁ ለየት ያሉ የባህል ሀብቶች በክልሉ መስተዋላቸውን ገልጿል፡፡ ባህላዊ እሴቶቹም የክልሉ ብሔረሰቦች የእጅ ስራ ውጤቶችና መለያ ምልክቶች መሆናቸውን ገልጾ የያንዳንዳቸው ምልክቶች መግለጫነት በዝርዝር አብራርቷል፡፡

ዋኢማ፣ "ለባህላዊ የአካባቢ አጠባበቅ መዳከም ግብረሰናይ ድርጅቶች ተጠያቂ ናቸው ተባለ፡፡" መስከረም 8/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62 ዓመት፣ ቁጥር 8፣ ገጽ-1

ለአገር በቀልና ባህላዊ የአካባቢ አጠባበቅ ዘዴዎች መዳከም መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎ ድርጅቶች ተጠያቂዎች መሆናቸውን የህይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማመልከቱን ገልጿል፡፡

ኢዜአ፣ "የኢትዮጵያ መንግስት ለባህል ቅርሶች ጥበቃና እውቅና ሰጥቷል፡፡" መስከረም 9/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣ ገጽ- 1

የኢትዮጵያ መንግስት ለባህል ቅርሶች ጥበቃና እውቅና መስጠቱን የወጣቶች፣ የስፖርትና ባህል ሚኒስትሩ ማስታወቃቸውን ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም የአክሱም ሐውልት በቅርቡ ወደ አገሩ እንደሚመለስ አንድ የኢጣሊያ ልዑካን ቡድን መሪ ማረጋገጣቸውን ገልጿል፡፡

------------ ፣ "የቤንሻንጉል ጉሙዝ ባህላዊ ቅኝት" (ክፍል ሁለት) ፣ መስከረም 12 /1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት ፣ ቁጥር 12፣ ገጽ -4

ባለፈው ሳምንት በዚሁ ርዕስ ስር ስለቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔርብሔረሰቦች በባህላቸው ውስጥ ያሉ ምልክቶችን መገለጫ

አንድ በአንድ ዘርዝሯል። በአሁኑ ደግሞ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔርብሔረሰቦችን የቀብር አፈጻጸም ስነስርዓት ገልጿል።

ኢዜአ፣ "የባህል ልውውጥን ለማዳበር የስእል ውጤቶች አስተዋጽኦ እንዳላቸው ተገለጸ።" መስከረም 23/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 23፣ ገጽ-1

በኢትዮጵያና በኢጣሊያ ህዝቦች መካከል ያለውን የባህል ልውውጥ ለማዳበር በወጣቶች የሚቀርቡ የሥነስዕል ውጤቶች የላቀ ድርሻ እንደሚኖራቸው በኢትዮጵያ የኢጣሊያ አምባሳደር ማስታወቃቸውን ገልጿል።

--------፣"የቻይና ባህላዊ ቡድን በኢትዮጵያ ትርዒቱ እንደሚያደርግ ተጠቆመ።" መስከረም 25/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62 ኛ ዓመት፣ ቁጥር 25፣ ገጽ -1

አስራአንድ አባላት ያሉት የቻይና ባህላዊ ቡድን ከመስከረም 27/1995 ዓ.ም ትርዒቱን በአዲስ አበባና በአዋሳ ከተሞች እንደሚያቀርብ የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ማስታወቃቸውን ገልጿል። ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰሞኑን የላከውን መግለጫ ጠቅሶ ኢትዮጰያና ቻይና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2008 ዓ.ም ቤጂንግ ላይ የተፈራረሙት የባህል ስምምነት አንዱ አካል የሆነውን ይህን ዝግጅት በብሔራዊ ቴያትር፣ በአፍሪካ ህብረት አዳራሽና በአዋሳ ከተማ በተለያዩ ጊዜያት ለህዝብ እንደሚቀርብ ገልጿል።

ስምረት ደመረ፣ "የኢትዮጵያ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦች የሚያስተዋውቅ ዶክመንተሪ ፊልም በቅርቡ ይፋ ይሆናል።" መስከረም 26/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 26፣ ገጽ-1

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የአገራችንን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈላጊ መስህቦችን ሊያስተዋውቅ የሚችል አንድ ወጥ ዶክመንተሪ ፊልም በቅርቡ እንደሚያስመርቅ አስታወቀ። በቢሮው የህዝብ ግንኙነት፣ ዶክመንቴሽንና ስልጠና አገልግሎት ኃላፊ አቶ ዮሐንስ አንዳርጌ ሰሞኑን ከጋዜጣው ሪፖርት ጋር ያደረጉትን ቃለምልልስም ጠቅሷል። በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውና በአራት ቋንቋዎች የተዘጋጀው ይህ ዶክመንተሪ ፊልም ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ለማራዘም፣ ከእነሱ የሚገኘውን ገቢ

በሚፈለገው መልኩ ለማኘትና የውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ከፍ እንዲል ለማድረግ የሚየስችል መሆኑን በቃለምልልሱ ገልጿል፡፡

ኢዜአ፣ "አርሷደሩን በባህላዊ ስፖርት ለማሳተፍ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ተጠየቀ፡፡" ጥቅምት 20/1995ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 50፣ ገጽ -10

የአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር አርሶአደሩን በባህላዊ ስፖርት ለማሳተፍ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ዝቅተኛ በመሆናቸው የየወረዳዎቹ ወጣቶች ባህልና ስፖርት ጽህፈት ቤቶች ለዚሁ የስፖርት ዘርፍ ትኩረት እንዲሰጡ መጠየቁን ገልጿል፡፡

ታረቀኝ ፈጠነ፡- "ዋርሳና ውርስ" ጥር 17 1995 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 42፣ ገጽ-4

የዋርሳና ውርስ ባህል በአብዛኛው በደቡብ ወሎ ዞን ከክርስቲያኑ ይልቅ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ይበልጥ የሚታይ መሆኑን ጠቅሶ በዞኑ ካሉት ወረዳዎች ውስጥ በተሁለደሬ ወረደ እጅግ ስር የሰደደ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ስለዋርሣና ውርስም በሰፊው ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "በኦስትሪያ በላንጊሎድስ ከተማ በኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ባህል ላይ ያተኮረ የስዕል ኢግዚብሽን ታየ፡፡" ህዳር 4/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 64፣ ገጽ-11

በኦስቲሪያ ላንጌሎድስ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በኢትዮጵያውያን ብሄር ብሄረሰበች ባህል ላይ ያተኮረ የስዕል ኤግዚቢሽን መቅረቡን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የገለጹትን ጠቅሷል፡፡

ታሪኩ ሀይሉ፡- "የባህል ህክምናው ከሣይንሣዊነት እርቆ እስከመቼ?" ህዳር 6/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 66፣ ገጽ 3

የኢትዮጵያ ህዝብ 80 በመቶው የሀገር በቀል ባህል ህክምና ተጠቃሚ መሆኑ እየተጠቀሰ ባለበት ባሁኑ ወቅት የህክምናውን አሰጣጥ ዘመናዊ ለማድረግና ሳይንሣዊ ዘዴን ለመከተል ግን

ድጋፍ እንደተደረገ ገልጿል፡፡ ለዚህም እንደ ችግር አድርጎ ያቀረበው የባህል መድሀኒት አዋቂዎች መድሀኒታችንን ብንሠጥ እንዘረፋለን ብሎ ዕፅዋቶችን በሚስጥር መያዝ እና የመድሀኒት ማጥኚያ ኢንስቲትዩቶች ደግሞ የዕፅዋቶቹን ምንነት መጀመሪያ ይዋለጹልን? በሚሉት ክርክር መግጠማቸውን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሀገራችን የባህል መድሀኒትና ህክምና ሊስፋፋና ሊዳብር አለመቻሉን ገልጿል፡፡

ቤተልሔም ክፍሌ፡- "ሥርዓተ ጾታን የሚያዳብሩ ልምዶችና ባህሎችን መዝግቦ ለትውልድ ማስቀመጥ እንደሚገባ ተጠቆመ፡፡" ታህሳስ 1/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 91፣ ገጽ-2

በሀገራችን ስርዓተ ጾታን የሚያዳብሩና የሚደግፉ በጐ ልማዶችንና ባህሎችን ለማጠናከርና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ተመዝግበው የሚቀመጡበት ሁኔታን ማመቻቸት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን እንደሚገባ የዓለም አቀፍ የገጠር ልማት ተቋም የአፍሪካ ሪጅን ዳይሬክተር ማስናተወቃቸውን ገልጿል፡፡ ዳይሬክተረ ዶክተር ይስሀቅ በቃሉ ትናንት በቀይ መስቀል ማሰልጠኛ ማዕከል በተካሄደው አውደ ጥናት ላይ ያደረጉት የመክፈቻ ንግግርን ጠቅሶ ሀገራችን በበርካታ በጐ ልማዶችና ባህሎች የበለጸገች መሆኗን ገልጿል፡፡ በሀገራችን በተለይም በሥርዓተ ጾታ ደጋፊ የሆኑ ልማዶችንና ባህሎችን ለማጐልበትና ለትወልድ ለማስተላለፍ ተመዝግበው የሚቃመጡበት ሥርዓት ሊኖር እንደሚገባ ማብራራታቸውን አያይዞ ገልጿል፡፡

ሰባሄ ካሣው ፡- "የልጃ ገረዶች ጀባታ በሠሜን ወሎ" ታህሳስ 5/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣ 62ኛ ዓመት፡ ቁጥር 95፣ ገጽ-12

በሰሜን ወሎ ዞን አንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች በተለይም በሀበሩ፣ ጉባላፍቶና ቆቦ ወረዳዎችና ዞኑን ከአፋር ክልል ጋር በሚያዋስኑ አንዳንድ ቀበሌዎች "ጀባታ" ባህል የተለመደ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ "ጀባታ" ማለት በነፃ የሚለገስ ወይም በስዕለት መልክ የሚቀርብ ስጦታ እንደሆነ የአካባቢው አዛውንቶች መናገራቸውን ገልጿል፡፡ በብዙ ቦታዎች አብዛኛውን ጊዜ በጀባታ መልክ የሚቀርቡት ጫት፣ ገንዘብና ልብስ እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች መሆናቸውን ገልፆ ከላይ በተጠቀሱት ቀበሌዎች ግን የሚቀረበው ጀባታ ከ15 ዓመት ጀምሮ ያሉ ልጃገረዶች መሆናቸውን አብራርቷል፡፡

ኢዜአ፡- "ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ለብልሽት ተዳርገዋል ተባለ"፡፡ ታህሳስ 8/1995 ዓ.ም ፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 98፣ ገጽ-5

በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል የሚገኙ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ተገቢውን ጥበቃ ስላልተደረገላቸው እየተበላሹ መሆኑን የአስተዳደር ካውንስሉ የትምህርት ባህል ጽህፈት ቤት ከትናንት በስቲያ ማስታወቁን ገልጿል፡፡ ለ2 ቀናት የተካሄደው የቅርስ ጉብኝት ኘሮግራም በተጠናቀቀበት ወቅት በጽህፈት ቤቱ የባህል ቡድን መሪ ወይዘሮ አስቴር ተሰማን ጠቅሶ የቱሪስት ማስህብ የሆኑት ታሪካዊ ባህላዊ ቅርሶች ለብልሽት የተጋለጡት ተገቢው ጥበቃ ስላልተደረገላቸው መሆኑን ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "በትግራይ አዳዲስ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እንዳሉ ተረጋገጠ፡፡" ታህሳስ 10/1995፣ አዲስ ዘመን፣62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 100፣ ገጽ-5

የትግራይ ክልል ቱሪዝም ቢሮ ለቱሪስቶች መስህብ በመሆን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት የሚያስችሉ አዳዲስ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች በጥናት ማግኘቱን እንዳስታወቀ ገልጿል፡፡ በቢሮው የቱሪዝም ማስፋፊያ ኃላፊ የሆኑትን አቶ ጀማል ከድርን ጠቁሞ ባለፈው ዓመት በክልሉ ሁሉም ዞኖች በተደረገ ጥናት ከአለት ተፈልፍለወ የተሰሩ ሀይማኖታዊ ሥፍራዎችን ጨምሮ ከ120 በላይ ታሪካዊ ቅርሶች መኖራቸው መረጋገጡን ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "የባህላዊ ቅርሶች መታሰቢያ ዓመት ዛሬ ተከብሮ ይውላል።" ታህሳስ 12/1995፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር102 ፣ገጽ-9

የባህላዊ ቅርቦች መታሰቢያ ደዓል ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ መከበሩን ጠቅሷል። የተባበሩት መንግስታት የአውሮፖውያኑ 2002 የባህላዊ ቅርሶች ዓመት ተብሎ እንዲጠራ በወሰነው መሠረት ዛሬ አዲብ አበባ ውስጥ በስብሰባ ማዕከል ለግማሽ ቀን ተከበሮ እንደሚማውል የወጣቶች ስፖርት ባህል ሚኒስቴር ማስታወቁን ገልጿል።

ስመኝ ግዛው፡- "የባህል ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልቶች የሚወያይ አውደጥናት ተጀመረ።" ታህሳስ 16/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ቁጥር 106፣ ገጽ-5

አገራችን ከ5 አመታት በፊት ባወጣቸው የባህል ፖሊስ ማስፈጸሚያ ስልቶች ዙሪያ የሚወያይ አውደጥናት ትናንት በጅማ ከተማ መጀመሩን ጠቁሟል። ለ3 ቀናት የሚቆየውን ይህንን አውደጥናት የተከፈቱት የወጣቶች ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስቴር አቶ መላኩ ጴጥሮስን ጠቅሶ ባለፉት ዓመታት የፖሊሲውን መሠረተ ሀሳብ ለተለያዩ አካላት የማብራራት ስራ ሊሰራ መቆየቱን እና ከዚህ ጎን ለጎንም ህሊሲውን በተለያዩ ቋንዎች አሳትሞ ለማሰራጨት መሞከሩን ገልጿል።

ኢዜአ፡-"የባህል ፖሊሲውን ለማስፈጸም የባለሙያ ስልጠና ያስልጋል ተባለ።"ታህሳስ 17/1995 ዓ.ም ፣አዲሰ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 107፣ገጽ-5

የተለያዩ የፌደራላዊ ፊፐብሊክ የባህል ፖሊሲን ለማስፈጸም ለሰው ሀይል ስልጠና ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ በፖሊሲው የማስፈጸሚያ ስልቶች ላይ የተወያዩ ባለሙየዎች ማመልከቻቸውን ገልጸዒል።

ዋኢማ፡- "ባለሙያዎቹ ባህልን ለማዳበር እንደሚጥሩ ገለጹ።" ታህሳስ 1995 ዓ.ም፣ አዲሰ ዘመን ፣62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 109 ፣ገጽ-2

አኩሪ ባህሎችን ለማሣደግና ለልማት ለማዋል በሚደረገው ጥረት የዜግነትና የሙያ ግዴታቸውን እንደሚወጡ የአምስት

ክፍሎች የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች መግልጻቸውን አስታውቋል፡፡ የኦሮምያ፣ ሶማሌ፣ ጋቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝና አፋር ክልሎች ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች ፡ "የባህል ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልቶች" በሚል ርዕስ በጅማ ከተማ ለ3 ቀናት ያካሄዱት አውደ ጥናት ከትናንት በስቲያ ሲያጠናቅቁ ባህላዊ እሴቶችንና ቅርሶችን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የባህል ፖሊሲውን ለህዝብ ለማስተዋወቅ ትኩረት ሰጥተው እንደሚንቀሳቀሱ መግለጻቸውን አስታውቋል፡፡

ኢዜአ፡- " የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባህል የሚያስተዋውቅ ሀገር አቀፍ ፌስቲቫል በቅርቡ እንደሚካሄድ ተጠቆመ፡፡ " ታህሣስ 24/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 114 ፣ገጽ-7

በስነጥበባትና በሌሎችም የባህል መስኮች አማካይነት የሚገለጹ የኢትያጵያን ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባህልን በአገር አቀፍ የባህል ፌስቲሻል አማካይነት የመተዋወቅያ እና የመቀራረቢያ መድረክ ለመፍጠር መታቀዱን የወጣቶች፣ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ማስታወቁን ገልጿል፡፡ በሚኒስቴሩ የባህል ትምህርት፣ ልማትና ግንኙነት ጊዜያዊ ኃላፊ አቶ በቀለ አበባውን ጠቅሶ በቅርቡ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሥነጥበባዊ እና ዕደ ጥበባዊ ሥራዎችን በጋራ በመከባበርና በእኩልነት በማስተናግድ በመካከላቸው መተዋወቅና መቀራረብ እንዲኖር ሀገር አቀፍ የባህል ፌስቲሻል እንደሚደረግ ጠቁሟል፡፡

----" የባህል ፖሊሲው እንዴት ይፈጸም?" ጥር 2/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 122፣ ገጽ-5

ሀገራችን የባህል ፖሊስ ካወጣች 5 ዓመታት አሳልፋለች፡፡ በዚህ ፖሊሲም ዘርፍ ብዙ ለሆኑ የኪነጥበብ ዘርፎች ትኩረት በመስጠት ለልማት፣ ለሠላምና በዴሞክራሲ ግንባታ ውስጥ ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዲችሉ ጉልህ ስፍራ ሰጥቷቸዋል፡፡

እናም ፖሊሲው በተግባር ሊውል ስለሚችልበት መንገድ የተወያየ አገር አቀፍ አውደጥናት  ባለፈው ታህሳስ ወር አጋማሽ

በጅማ ከተማ ተካሂዶ እንደነበረ ጠቅሶ በዘህ አውደ ጥናት ላይም በመዚቃና በዳንስ ጥበባት በአብያተ መጽሃፍት፣ በቅርሶች፣ በስዕልና፣ በዕደ ጥበባት፣ በቴያትርና በሲኒማ ጥበባት፣ በስነቃልና በስነፅሁፍ፣ በቋንቋ እንዲሁም ባህልን መሠረት ያደረገ የልማት አቅጣጫ በሚሉና በተመሣሣይ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ወረቀቶች ቀርበው ውይይት መካሄዱን ገልጿል፡፡ የጥናት ወረቀቶቹን አብይ ቁም ነገሮችም አቅርቧል፡፡

----------“የባህል ፖሊሲው እንዴት ይፈጸም “ጥር 27/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 147 ፣ገጽ-5

ባለፈው ሣምንት በተጠቀሰው አውደ ጥናት ላይ የቀረቡትን ጥናታዊ ጽሁፎች ዝርዝር በቀጣይነት እያንዳንዳቸውን አብራርቷል፡፡

ደረጀ ተድላ፡- “አራተኛው አገር አቀፍ የባህል ስፖርት ፌስቲቫል በኣሮሚያ ክልል የበላይነት ተጠናቀቀ፡፡” የካቲት 19/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 169፣ ገጽ-12

ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ በአሰላ ከተማ አረንጓዴ ስታዲየም ሲካሄድ የቆየው አራተኛው አገር አቀፍ የብሄር ብሄረሰቦች ባህላዊ ስፖርት፣ ትርኢት፣ ጨዋታና ውድድር ባለፈው እሁድ በኦሮሚያ ክልል የበላይነት መጠናቀቁን ገልጿል፡፡ የኦሮሚ ክልል የአጠቃላይ ውጤት ዋንጫ ተሸላሚ ሊሆን የቻለው በገና፣ ለባለ12 ጉርጓድ ገበጣና በፈረስ ጉግስ ውድድሮች አሸናፊ በመሆን ነው ሲል ገልጿል፡፡

ዋኢማ፡- “ግጥሞችን በሰላም ለመፍታት ባህላዊ የውይይት መድረኮችን ማጠናከር እንደሚገባ ተጠቆመ፡፡” የካቲት 22 ቀን 1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 172 ፣ገጽ-9

በደቡብ ክልል በህዘቦች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ ባህላዊ የውይይት መድረኮችን ማጠናከር እንደሚገባ መገለጹን ዘገግቧል፡፡ በአዋሣ ከተማ “ ትራይዳይሜንሽናል ቪው” የተባለ አገር በቀል ድርጅት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያዘጋጀውን የግጭት አፈታት

ሥልጠና ከትናንት በስትያ ሲጀምር የክልሉ ፍትህ ቢሮ ሀላፊ  አቶ ብርሃኑ አዴሎ ያሉትን ጠቅሶ ባህላዊ የውይይት መድረኮችን ማጠናከር በህዝቦች መካከል ሰላማዊ ጉርብትናን ለመፍጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጿል፡፡

ኢዜአ፡- "በባህል መድሀኒት እናድናለን ብለው ለግለሰቦች መሞት ምክንያት የሆኑ ተያዙ፡፡" መጋቢት 5/1995 ዓም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 185 ፣ገጽ-5

በምስራቅ ሀረርጌ በጉለ አዳና በጎሮጉቱ ወረዳዎች በባህል መድሀኒት እናድናለን ብለው ለሁለት ሰዎች መሞት ምክንያት የሆኑ 3 ግለሰቦች እንደተያዙ ፖሊስ ማስታወቁን ገልጿል፡፡ ጉለአዳ ወረደ ውስጥ የዕጢ መድሀኒት ያሰረው የባህል መድሀኒት አዋቂ ነኝ ባይ በማግስቱ እንዲቀይር ተጠቅቆ ፈቃደኛ ባለመሆኑ መድሀኑቱ አቃጠለኝ ይድረቅልኝ ያለው ህመምተኛ ተደብቆ ግለሰቡ መኖሪያ ቤት በመግባቱ የተቀመጠ የቅጠላ ቅጠል ጭማቂ ወስዶ በሌላ ሰው አማካይነት አራት ሲሪንጅ ወግቷቸው የተወጉት ሰዎች መሞታቸውንና አጠቃላይ ሁኔታው በመጣራት ላይ መሆኑን ፖሊሶች ማስታወቃቸውን ዘግቧል፡፡

ዋኢማ፡- "መምሪያው አንድ ሺህ ስድሰት መቶ ሃምሳ (1650) ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን አሰባሰበ"፡፡ መጋቢት 10/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 190 ፣ገጽ-2

የምስራቅ ወነገ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ 1ሺ 650 ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ማሰባሰቡን አስታውቋል፡፡ በመምሪያው የባህል ቡድን መሪ አቶ ቸርነት ዋቆያ ሰሞኑን የገለጹትን አስመልክቶ የዞኑን ህዝብ ታሪካዊ አኗኗር እና ባህል የሚያንጸባርቁ ቅርሶች የተሰበሰቡት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገ ጥረት መሆኑን ገልጿል፡፡ ባህላዊ ልብሶሽ፣ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ፣ ከእንጨትና ብረታ ብርት የተሰሩ ቅርጻቅርጾችና ጥንታዊ የብራና ጽሁፎች ከተሰበሰቡት ቅርሶች ዋና ዋና መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡

ኢዜአ፡- "የኦሮሞ ልማት ማህበርን በገንዘብ ለማጠናከር በጅዳ ባህላዊ የሙዚቃ ዝግጅት ተካሄደ ። " መጋቢት 11/1995 ዓ.ም፣ 62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 191 ፣ገጽ-7

የኦሮሞ ልማት ማህበርን በገንዘብ ለማጠናከር በጅዳ ባህላዊ የሙዚክ ዝግጅት መካሄዱን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስታወቁን ገልጿል። ሚኒስቴሩ ከትናንት በስቲ የገለጸውን አስመልክቶ በማህበሩ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴና ጂዳ በሚገኘው ቆንስላ ጽህፈት ቤት ትብብር በተካሄደው የሙዚቃ ዝግጅት 10 ሺህ የሳውዲ ሪያል ገቢ መገኘቱን ገልጿል። በተጨማሪም በጅዳ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች ወደ አገራቸው ሲገቡ የለማችና ያደገች ኢትዮጵያን ለማየት አገር ቤት በሚካሄደው እንቅስቃሴ መሣተፍ እንደሚኖርባቸው ማሳሰባቸውን ገልጿል።

ዋኢማ፡- "የብሄር ብሄረሰቦችፀ ህዝቦች ባህል የሚያንጸባርቅ ሀገር አቀፍ ፌስቲቫል ዝግጀት ተጀመረ።" መጋቢት 22/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 26ኛ ዓመት፣ ቁጥር 202፣ ገጽ-2

በወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር አዘጋጅነት የሁሉም ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህል ሴክተር ቢሮዎች የሚሳተፍበት አአንድ ሀገር አቀፍ የባህል ፌስቲቫል ዝግጀት መጀመሩን የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ማስታወቁን ገልጿል። በፌስቲቫሉ ላይ የባህላዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ ትርኢት፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦት የሙዚቃ መሣሪዎች፣ የባህላዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ አልባሣት፣ ትውፊታዊ ስዕል የስዕል መሣሪያዎች የሚቀርቡበት መሆኑንና ፌስቲቫሉ በአቀራረቡ የተለየ ሀገር አቀፍ ይዘት እንደሚኖረው መጠቆሙን ገልጿል።

ስመኝ ግዛው፡- "የባህል ፌስቲቫሉ ሳይከፈት ቀረ። "ሚያዝያ 14/1995ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 224 ፣ገጽ-1

በኢትዮ ካልቸራል ኘሮሞሽን አዘጋጅነት ለ10 ቀናት ይቆያል ተብሎ የታሰበው "ኢትዮ-ባህል ሳምንት 95" ፌስቲቫል

በኤግዚቢሽን ማዕከልና በኘሮሞሽን መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ሳይከፈት መቅረቱን ገልጿል፡፡

ጌታነህ ፅጌ "የተስተጓጐለው የባህል ኢግዚቢሽን ዛሬ ይከፈታል" ሚያዝያ 16/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 226 ፣ገፅ -1

በአዲስአበባ ባህል ማዕከልና በኢትዮ- ካልቸራል ኘሮሞሽን መካከል በተፈጠረው አለመግባባት የተነሣ የተስተጓጐለው የባህል ፌስቲቫል ዛሬ እንደሚከፈት የአዲስ አበባ ባህል ማዕከል ዋና ስራ አስኪያጅ ወ/ሪት መቅደስ ገብረ መድህንና የኢትዮ- ካልቸራል ኘሮሞሽን ሀላፊ አቶ ሙራድ መሀመድ በአንድነት መግለጻቸውን አስታውቋል፡፡

ጌታነህ ፅጌ "በህዝቦች ባህልና አኗኗር ላይ በመመስረት ወደ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማምራት እንደሚችል ተገለጸ፡፡ " ሚያዝና 17/1995 ዓ.ም፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 227፣ ገጽ-1

በህዝቦች ባህልና አኗኗር ላይ በመመስረት ወደፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማምራት የአገሪቱን መልካም ባህል በስፋት በማስተዋወቅ ወጣቱን ትውልድ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ ካስገደደው የባህል ወረራ ማላቀቅ እንደሚችል ገልጿል፡፡ መንግስት በባህል ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያወች ለሚያደርጉት ጥረት ድጋፍ እንዲሰጥ መጠየቁንም አያይዞ ገልጿል፡፡

ወንድሙ ኃይሉ፡- "ባህላዊ ቅኝት በኮሞ ብሔረሰብ" ሚያዝያ 21/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62 ዓመት ፣ቁጥር 231 ፣ገጽ-5

"ኮሞ" የሚለው ስያሜ የተገኘው ብሄረሰቡ ከሌሎች ጋር ከተነሣበት ግጭት ራሱን በማግለሉ ነው፡፡ ኮሞ ማለት "መለየት" ከሚለው ጋር ተመሣሣይ ትርጉሜ ያለው መሆኑን ጠቅሶ ይህን ስያሜ ከማግኘታቸውነው በፊት "ጀነብያን" /ደቡባውያን/ ይባሉ እንደነበር ጠቁሟል፡፡ በባህላዊ ስርዓታቸውም ዙሪያ ሰፊ ገለጻ አድርጓል፡፡

ስመኝ ግዛው፡- “የሀገራችንን ባህል የሚያስተዋውቅ ትርዒት በአውሮፖውያን አሜሪካ” ሰኔ 3/1995 ዓም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት ቁጥር 273፣ በገጽ 5

ሰሞኑን የኢትዮጵያን ትክክለኛ የባህል ጭፈራዎችና አልባሳት የሚያስተዋውቅ የባህል ቡድን በአሜሪካና አውሮፖ ሀገሮች ተዘዋውሮ ትዕይንቱን እንዳቀረበ ገልጿል፡፡ ዝግጅቱን ያስተባበረው ጌትሽ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኢንተርኘራይዝ ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳዊት ጌታሁን የገለጹትን አስመልክቶ በባህላዊ ሙዚቃዎች ላይ የሚታዩ ድክመቶች እንዲታረሙ ከፍተኛ ጥረት እንደተደረገም ገልጿል፡፡ ይህ የባህል ቡድን በተለያዩ የአውሮፖ፣ አሜሪካ ና የአፍሪካ ሀገሮች ተዘዋውሮ የኢትዮጵያን የባህል ውዝዋዜና አለባበስ እንደሚያሳይ ገልጿል፡፡

ኢዜአ “የባህል መድሀኒት ህክምና አዋቂዎች ማህበር የዕፅዋት ዘር ማልሚያ ቦታ ተረከበ”፡፡ ሰኔ 3/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 273፣ ገጽ-7

የሰሜን ጐንደር የባህል መድኃኒትና ህክምና አዋቂዎች ማህበር ለመድሀኒት የሚውሉ እጽዋት ዝርያዎች የሚያለማበት ሁለት ሺ አምስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ከከተማው ማዘጋጃ ቤት ማግኘቱን አስታውቋል፡፡ የማኀበሩ ሊቀመንበር መሪ ጌታ ሄኖክ አየነውን ጠቅሶ ማኀበሩ ሰሞኑን ከመዘጋጃ ቤቱ በነጻ ባገኘው በዚሁ ቦታ ላይ እየጠፉ የመጡትን የ60 በላይ የእፅዋት ዝርያዎችን ለማልማት በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጿል፡፡

ዋኢማ ፣ “የባህል ልማት ዘርፉ በሰለጠነ የሰው ሃይል አለ መኖር እንደተዳከመ ሚኒስትሩ አመለከቱ፡፡ ” ሰኔ 6/1995 ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 276 ገጽ-2

ለባህል ልማትና እድገት መኀልበት አጋዥነት ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመኖር ለዘርፍ መዳከም መንስኤ መሆኑን የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ መግለጻቸውን አስታወቀ፡፡ አራተኛው ሀገር አቀፍ የባህል ጉባኤ ትናንት በአርባ ምንጭ ሲከፈት በሃገሪቱ የባህል ልማትና ዕድገትን ለማምጣት የሚቻለው በግንባር

ቀደምትነት በባህል ዘርፍ በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል ሲገኝ መሆኑን ሚኒስትሩን ጠቅሶ ገልጿል።

ዋኢማ "የባህል ዘርፉ መጎልበት ለዴሞክራሲ ግንባታ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ተመለከተ። ሰኔ 9/1995 ዓም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ ዓመት ፣ቁጥር 279 ፣ገጽ-2

የባህል ዘርፍ መጠናከር ለሀገራዊ የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው የወጣቶች ስፖርት ባህል ሚኒስትር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ማመልከታቸውን ገልጿል። የባህል ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶበት እንዲጠናከር መደረጉ ለሠላም ለልማትና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የላቀ ፋይዳ እንዳለው ሚንስትሩ በአርባምንጭ በተዘጋጀው አራተኛው አገር አቀፍ ባህል ጉባኤ ላይ መግለጻቸውን አስታውቋል።

ዑስማን መሀመድ፣ "የባህላዊ ህክምና ህግ ማውጣት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ተመለከተ። "ሰኔ24/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 294፣ ገጽ-1

ባህላዊ ህክምናን ከዘመናዊ የጤና አጠባበቅ ስርዓት ግር ለማቀናጀት የባህላዊ ህክምና ህግ ማውጣት አቢይ ጉዳይ መሆኑን የኢትዩጵያ ሥርና ስነ-ምግግ ምርምር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ዶክተር አበራ ግደይ መግለጻቸውን አስታውቋል። የባህላዊ ህክምና ህግ አለመኖር ባህላዊ ህክምናን ከመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ጋር ለማዋሀድ መሰናክል ሆነው ከቆዩ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው መሆኑን ጠቅሶ የህጉ መውጣት ደግሞ ወሣኝ መሆኑን ማመልከታቸውን ገልጿል። ከዚህም ጋር አያይዘው ትክክለኛ አሰራር ብለው የመዘገቧቸው ነገሮች አሠራር የሚጸድቅበት ስርዓት አስፈላጊ መሆኑን አብራርቷል።

ኢዜአ፡- "የኢትዮጵያና የግብጽ የቆየ ወዳጅነት በንግድና በባህል ልውውጥ ሊጠናከር እንደሚገባ ተገለጸ።" ሰኔ 27/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 297፣ ገጽ-1

በኢትዮጲያና በግብጽ መካከል ንግድን በማስፋፋትና የባህል ልውውጥን በማጠናከር የቆየ ወደጅነታቸውን ይበልጥ ማጠናከር እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ማስታወቃቸውን

ገልጿል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአልሀረም ጋዜጣ ጋር ከትናንት በስቲያ አዲስ አበባ ውስጥ ያደረጉትን ቃለ ምልልስ አስመልክቶ ሁለቱ አገሮች ዓባይ ወንዝ ያስተሣሠራቸው ወዳጅ አጋሮች መሆናቸውንን ይህንኑ ግንኙነታቸውን በሌሎች ዘርፎች ማጠናከር እንደሚጠበቅባቸውም ገልጿል፡፡

ዑስማን መሀመድ ፡- “ የባህል ህክምናን ህጋዊ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ መንግስት የጀመረው ጥረት ተደነቀ፡፡” ሰኔ 27/1995፣ አዲስ ዘመን፣ 62 ኛ ዓመት ፣ ቁጥር 297፣ ገጽ-5

የባህል ህክምናን የመንግስታዊ ተቋም አካል ለማድረግና የህክምና አዋቂዎችን ተግባር ለመቆጣጠር እንዲሁም የህክምናው ተጠቃሚ የሆነውን የህብረተሰብ ደህንነት ለመጠበቅ የተጀመረው ጥረት አበረታች መሆኑን የተለያዩ የህክምና አዋቂዎችን ጠቅሶ ገልጿል፡፡

ስመኝ ግዛው፣ “ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ዘላቂነት እንዲኖራቸው…” ሐምሌ 1/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 301፣ ገጽ-5

የሀገራችን ባህላዊ መዚቃ መሣሪያዎች ለመጠቀም አስቸጋሪ ናቸው፡፡ ይህን ችግር ከመሠረቱ ለመቅረፍና ባህላዊ መሣሪያዎቹ የህዝብ ሀብት እንዲሆኑ በማሠብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት የባህል ሙዚቃ መምህር የሆኑት አቶ አለማየሁ ወልደ ዮሀንስ መፍትሄ እንደፈለጉለት ገልጿል፡፡ ማለትም በማሲንቆ፣ በዋሽንትና በበገና አጨዋወት ላይ ሰዎች ያለአስተማሪ ራሳቸውን በእራሳቸው እንዲያስተምሩ መሰረታዊ የእውቀት መገብያ መጻህፍቶችን መጻፋቸውን ጠቅሶ ለ22 ዓመታት በሙያው የቆዩትን በባህላዊ ሙዚቃዎች በህይወት ልምዳቸው ዙሪያ አነጋግሮ ከልምዳቸው ያወጉትንም አካቶ አቅርቧል፡፡

--------- “ባህላዊ ገጽታዎች በአይዳ ብሄረሰብ” ሐምሌ 15/1995 ዓ.ም.፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 355፣ ገጽ-5

የአይዳ ብሄረሰብ የሚገኘው ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ኦሞ ዞን በጐፋ ዙሪያ ወረዳ ነው፡፡ ይህን ብሄረሰብ በሰሜንና በሠሜን ምስራት ጐፋ፣ በደቡብና በምዕራብ አሪ፣ በምስራቅ ዑባምሌ እንደሚያዋስኑ ገልጾ የዚህን ብሄረሰብ አሰፋፈር የብሄረሰቡን ቋንቋ ምደባ፣ የህዝብ ብዛት፣ የስያሜውን አሰጣጥ ወዘተ ገልጿል፡፡

------------- "ባህላዊ የሸክላ ጥበብ በአሊያንስ" ነሐሴ 13/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ ዓመት፣ ቁጥር 343፣ ገጽ-5

በሀገራችን የሸክላ ውጤቶችን ለማሣደግ አንዳንድ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን ጠቅሶ በቅርቡም በአልያንስ እትዮ ፍራንሲስ ክረምቱ እስከሚገባደድ ለህዝብ ክፍት ሆኖ የሚቆይና በወይዘሮ ንጋቷ የተመረቱ የሸክላ ስራ ውጤቶች ለእይታ መብቃታቸውን ገልጿል፡፡

## 3.2 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከ1994-1995 ዓ.ም የወጡ ባህል ነክ ፅሁፎች ዝርዝር በደራሲዎች ስም ቅደም ተከተል

*መስፍን አብርሃ "የባህል እንክብካቤ በትግራይ" ሰኔ 2 1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፤61ኛ አመት ፣ቁጥር 272፣ ገፅ-4*

*ሰለሞን ተስፋዬ ፣"የኢትዮ ቻይና ግንኙነት ታሪካዊና ባህላዊ ትብብር እንዳለው ተመለከተ። " አዲስ ዘመን፤ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 22፣ መስከረም 22/1994 ዓ.ም፣ ገፅ-1*

*ሰለሞን ጥዑመልጣን፣ "በአፋር ክልል በ18 ሚሊዮን ብር ወጪ የባህል ማዕከልና ሙዚየም ሊገነባ ነው።" መጋቢት 6 1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 186 ፣ገፅ-1*

*ስምረት ደመረ፣ "የኢትዮጵያን ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦች የሚያስተዋውቅ ዶክመንተሪ ፊልም በቅርቡ ይፋ ይሆናል።" መስከረም 26 1995 ዓ.ም ፣ኢዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 26፣ ገፅ-1*

*ስመኝ ግዛው ፣"የሀገራችንን ባህል የሚያስተዋውቅ ትርዕይት በአውሮፓና በአሜሪካ " ሰኔ 3/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 273 ፣ገፅ-5*

*ስመኝ ግዛው ፣" ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎቻችን ዘላቂነት እንደሚኖራቸው " ሀምሌ 1/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 301፣ ገፅ-5*

*ቤተልሄም ክፍሌ፣ " ስርዓተ ፆን የሚያዳብር ልምዶችና ባህሎችን መዝግቦ ለትውልድ ማስቀመጥ እንደሚገባ ተጠቆመ።" ታህሳስ 1/1995፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 91 ፣ገፅ-2*

*ቤተልሄም ክፍሌ፣ "በባህላዊ ህክምና ለተሰማሩ ሴቶች ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተጠቆመ።" ሰኔ 7/1994፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ፣ቁጥር 277 ፣ገፅ-5*

*ቤተልሄም ክፍሌ፣" ባህላዊ ተፅእኖዎች በኩለሜ ቤሄረሰብ" ህዳር 1/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 61 ፣ገፅ-10*

*ታምሩ ወ/ሚካኤል፣" ለባህል ስፖርት ብሄራዊ ዳኞች ስልጠና ተሰጠ።" ህዳር 28/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 88፣ ገፅ-9*

ታምሩ ወ/ሚካኤል፣“ በገና ዕለት ባህላዊ ስፖርት ጨዋታዎች ተካሄዱ ፡፡” ጥር 1/1994 ዓ.ም ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 121 ፣ገፅ-10

ታምሩ ወ/ሚካኤል ፣ “የባህል መዕከል ለባህላዊ ሙዚቃ” መስከረም 6/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 6 ፣ገፅ-4

ታደለ ገድለ፣“ የመስቀል በዓልና አከባበር በሀድያ” መስከረም 13/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 13፣ ገፅ-4

ታደለ ገድሌ፣“ የባህል ግንባታ ከባህል ፖሊስ አንፃር” ግንቦት 25/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 265 ፣ገፅ-4

ታደለ ገድሌ፣“ ባህልንና ወዳጅነትን የሚጠናክር የስዕል ኤግዚብሽን ” ሰኔ 9/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 279 ፣ገፅ-4

ታደለ ገድለ፣“ የባህል ፖሊሲው ከሲኒማ ጥበብ አንፃር ”ሰኔ 2/1994 ዓ.ም፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 272 ፣ገፅ-4

ታረቀኝ ፈጠነ፣ “ዋርሳና ውርስ” ጥር 17/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 42 ፣ገፅ-4

ታሪኩ ሀይሉ፣“ የባህል ህክምናው ከሳይንሳዊነት እርቆ እስከ መቼ” ህዳር 6/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 66 ፣ገፅ-3

አማረች ተሰማ፣“ ባህልና ወግ ተረሳ እንዴ? ” የካቲት 10/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 160፣ ገፅ-4

አያሌው ንጉሴ፣ “ በባህል ዘርፍ ላ በዲፕሎማ ደረጃ ትምህርት ለመጀመር የሚያስችል ረቂቅ ጥናት ቀረበ፡፡” ግንቦት 30/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 270፣ ገፅ-3

አያሌው ንጉሴ፣ “ የባህል ጉባኤው ለባህል ዕድገት” ሰኔ 16/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 286፣ ገፅ-4

ኢዜአ፣ “በበዓሉ ዋዜማ ሳምንት ከ701 ሚሊዮን ብር በላይ ከባንክ ወጥቷል፡፡” መስከረም 1/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 1 ፣ ገፅ-1

ኢዜአ፣“ በደቡብ ወሎ ዞን የባህል መድሀኒት አዋቂዎች ማህበር ተቋቋመ፡፡” መስከረም 9/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ፣ቁጥር 9 ፣ገፅ-5

ኢዜአ፣“ ሴቶች በባህል ተፅእኖ የልፋታቸው ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ተገለፀ፡፡” ጥቅምት

13/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 9 ፣ገፅ-4

ኢ.ዜአ፣“ በወጣቶች ባህልና ስፖርት ዙሪያ ውጤታማ ተግባር ለማከናወን ጥናት ይደረጋል።” ህዳር 21/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 81 ፣ገፅ-1

ኢ.ዜአ፣“ የትዕይንት ጎንደር የስፖርትና የባህል ፌስቲቫል ተጀመረ።” ጥር 9 /1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቀጥር 126፣ ገፅ-8

ኢ.ዜአ፣“ የትዕይንት ጎንደር የስፖርትና ባህል ፌስቲቫል ተጠናቀቀ።” ጥር 15/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 126 ፣ገፅ-8

ኢ.ዜአ፣“ በሰሜን ወሎ ባህላዊ የስፖርት ውድድር እየተካሄደ ነው።” መጋቢት 1 ቀን 1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 181፣ ገፅ-11

ኢ.ዜአ፣“ በሀረር ከተማ የባህልና የንግድ ትርኢት ሊካሄድ ነው።” መጋቢት 12/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 192 ፣ገፅ-6

ኢ.ዜአ፣“ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት 20 ሺህ ብር እና ባህላዊ ስዕል ተበረከተ።” ግንቦት 3/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር243 ፣ገፅ-5

ኢ.ዜአ፣“ የጀርመን የባህል ተቋም 40ኛ አመቱን እደሚያከብር ተመለከተ።” ግንቦት 28/ 1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 264 ፣ ገፅ-1

ኢ.ዜአ፣“ የጀርመን የባህል ኢንስቲትዩት የተመሰረተበትን 40ኛ አመት ተከበረ።” ግንቦት 28/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 268 ፣ገፅ-1

ኢ.ዜአ፣“ በወሊሶ የብሄር ብሄረሰቦችን ባህላዊ ህይወታዊ ሀብቶች የሚሳይ ኤግዚቢሽን ሊከፈት ነው።” ሰኔ 29/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 314፣ ገፅ-5

ኢ.ዜአ፣“ የክርስቲያንና የሙስሊሙን የሙዚቃ ባህል ለማስተዋወቅ የሚያስችል ሲምፖዚየም ሰሞኑን ይካሄዳል። ”ሐምሌ 14/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 314፣ ገፅ-5

ኢ.ዜአ፣“ የኢትዮጵያ መንግስት ለባህል ቅርሶች ጥበቃና እውቅና ሰጥቷል። ”መስከረም 9/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 9 ፣ገፅ-1

ኢ.ዜአ፣“ የባህል ልውውጥን ለማዳበር የስዕል ውጤቶች አስተዋፅኦ እንዳላቸው ተገለፀ።” መስከረም 23/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 23፣ ገፅ-1

ኢ.ዜ.አ፣“ አርሶ አደሩን በባህላዊ ስፖርት ለማሳተፍ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ተጠየቀ።”፣ ጥቅምት 20/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 10፣ ገፅ-10

ኢ.ዜ.አ፣“ በኦስትሪያ በላንጊሎጅሽ ከተማ በኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ባህል ላይ ያተኮረ የስዕል ኤግዚብሽን ታየ።” ህዳር 4/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 64 ፣ ገፅ-11

ኢ.ዜ.አ፣“ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ለብልሽት ተዳርገዋል ተባለ።” ታህሳስ 8/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 95 ፣ገፅ-5

ኢ.ዜ.አ ፣ “በትግራይ አዳዲስ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እንዳሉ ተረጋገጠ ።” ታህሳስ 10/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 100፣ ገፅ-5

ኢ.ዜ.አ፣“ የባህላዊ ቅርሶች መታሰቢያ አመት ዛሬ ተከብሮ ይውላል ።” ታህሳስ 12/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 102 ፣ገፅ-9

ኢ.ዜ.አ፣“ የባህል ፖሊሲውን ለማስፈፀም የባለሙያ ስለጠና ያስፈልጋል ተባለ። ” ታህሳስ 17/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት፣ ቁጥር 107 ፣ገፅ-5

ኢ.ዜ.አ፣“ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባህልን የሚያስተዋውቅ ሀገር አቀፍ ፌስቲቫል በቅርቡ እንደሚካሄድ ተጠቆመ። ” ታህሳስ 24/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት፣ ቁጥር 114 ፣ገፅ-7

ኢ.ዜ.አ፣“ በባህል መድሀኒትእናድናለን ብለው ለግለሰቦች መሞ ት ምክንያት የሆኑ ተያዙ።” መጋቢት 5/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 185 ፣ ገፅ-5

ኢ.ዜ.አ፣“ የኦሮሞ ልማት ማህበርን ለማጠናከር በጅዳ ባህላዊ የሙዚቃ ዝግጅት ተካሄደ።” መጋቢት 11/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 191፣ ገፅ-7

ኢ.ዜ.አ፣“ የባህል መድሀኒት ህክምና አዋቂዎች ማህበር የዕፅዋት ዘር ማልሚያ ቦታ ተረከበ።” ሰኔ 3/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 273 ፣ገፅ-7

ኢ.ዜ.አ፣“ የኢትዮጵያና የግብፅ የቆየ ወዳጅነት በንግድና በባህል ልውውጥ ሊጠናከር እንደሚገባ ተገለፀ።”ሰኔ 27/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 297፣ ገፅ-1

ወንድሙ ሀይሉ፣“ባህላዊ ቅኝት በኮሞ ብሄረሰብ” ሚያዝያ 21/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት፣ ቁጥር 235፣ ገፅ-5

ዋኢ.ማ፣"ባህላዊ መድሀኒቶች በዘመናዊ መልኩ ተዘጋጅተው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተጠየቀ።" መስከረም 23/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 23 ፣ገፅ-6

ዋኢ.ማ፣" ባህላዊ የእፅዋት መድሃኒት ምርምር ተቋም ተቋቋመ።" ህዳር 23/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 69 ፣ገፅ-6

ዋኢ.ማ፣"ቤተ ጉራጌ ባህል ማዕከል በብሄረሰቡ ተወላጆች ሊቋቋም ነው።" ህዳር 23/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 71 ፣ገፅ-6

ዋኢ.ማ፣"የአፋር ባህላዊ ቅርሶች ማሰባሰቢያ ማዕከልና ሙዚየም ሊገነባ ነው ተባለ።" ህዳር 26/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ፣ቁጥር 88 ፣ገፅ-3

ዋኢ.ማ፣" የባህል ወረራን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመካሄድ ላይ ይገኛል።" ታህሳስ 1/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ቁጥር 91 ፣ገፅ-7

ዋኢ.ማ፣"ባህላዊ ወርቅ አምራቾችን በማህበር ለማደራጀት የተደረገው ውጤት ሳይሳካ ቀረ።" መጋቢት 1/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 197 ፣ገፅ-12

ዋኢ.ማ፣"የዕደ ጥበብና ባህላዊ እቃዎች ለገበያ ስለሚውሉበት መንገድ እየተጠና ነው። " ሚያዝያ 215/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ቁጥር 225፣ገፅ-5

ዋኢ.ማ፣"በበርታ ብሄረሰብ አባላት ለሚዘወተር ባህላዊ አደን የዱር እንስሳት ቁጥር ተመናመነ።" ግንቦት 4/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 244፣ ገፅ-6

ዋኢ.ማ፣"ለባህላዊ የአካባቢ አጠባበቅ መዳከም ግብረሰናይ ድርጅቶች ተጠያቂ ናቸው ተባለ።" መስከረም 8/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 8 ፣ገፅ-1

ዋኢ.ማ፣" ባለሙያዎቹ ባህልን ለማዳበር እንደሚጥ ሩ ገለፁ።" ታህሳስ 19/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 109 ፣ገፅ-2

ዋኢ.ማ፣" ግጭቶችን በሰላም ለመፍቱ ባህላዊ የውይይት መድረኮችን ማጠናከር እንደሚገባ ተጠቆመ።" የካቲት 22/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት፣ ቁጥር 172፣ ገፅ-9

ዋኢ.ማ፣" መምሪያው አንድ ሺ 650ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን አሰባሰበ ።" መጋቢት 10/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 190 ፣ገፅ-2

ዋኢማ፣“ የብሄር ብሄረሰቦችና የህዝቦች ባህል የሚያንፀባርቅ ሀገር አቀፍ ፌስቲቫል ዝግጅት ተጀመረ፡፡” መጋቢት 22/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 202 ፣ገፅ-2

ዋኢማ፣“ የባህል ልማት ዘርፉ በሰለጠነ የሰው ሃይል አለመኖር እንደተዳከመ ሚኒስትሩ አመለከቱ፡፡” ሰኔ 6/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 276፣ ገፅ-2

ኡስማን መሃመድ፣“ የባህላዊ ህክምና ህግ ማውጣት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ተመለከተ፡፡” ሰኔ 24/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 294፣ ገፅ-1

ኡስማን መሃመድ፣“ የባህል ህክምናን ህጋዊና ተቋማዊ መሰረት ለማስያዝ መንግስት የጀመረው ጥረት ተደነቀ፡፡” ሰኔ 27/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 297 ፣ገፅ-5

ደረጀ ተድላ፣“ አራተኛው አገር አቀፍ የባህል ስፖርት ፌስቲቫል በኦሮሚያ ክልል የበላይነት ተጠናቀቀ ፡፡” የካቲት 19/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 62ኛ አመት ፣ቁጥር 169 ፣ገፅ-12

ጌታቸው ሰናይ፣“ ህይወታዊ ሃብትን መንከባከብ ለባህላዊ እሴት ጥበቃ” መስከረም 1/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 1 ፣ገፅ-2

ጌታቸው ሰናይ፣“ ባህላዊ ውበት- በወሊሶ” ሐምሌ 29/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 329፣ ገፅ-6

ጌታነህ ፅጌ፣“ የተስተጓጎለው የባህል ኤግዚቢሽን ዛሬ ይከፈታል ፡፡” ሚያዝያ 16/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 226፣ ገፅ-1

ጌታነህ ፅጌ፣“ በህዝቦች ባህልና አኗኗር ላይ በመመስረት ወደ ፈጣን የኢኮኖሚእድገት ማምራት እንደሚቻል ተገለፀ፡፡” ሚያዝያ 17/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 227፣ ገፅ-1

ጌትነት ገሰሰ፣ “የኢትዮ- አረብ የባህል ሳምንት ከመጪው አርብ ጀምሮ ይከበራል፡፡” ግንቦት 24/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ፣ቁጥር 264 ፣ገፅ-1

ፀሃይ ለማ፣“ ባህላዊ ጋብቻ በሶዶ ክስታኔ” ሚያዝያ 27/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት ፣ቁጥር 237 ፣ገፅ-4

ፈይሰል ኢብራሂም መሃመድ፣ “ የሃረሪ ብሄረሰብ ባህላዊ ጋብቻ” ነሀሴ 5/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት፣ ቁጥር 335፣ ገፅ-5

------------ ፣ “የጌዲዮ ብሄረሰብ ባህላዊ ቅኝት” መስከረም 6/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 6 ፣ገፅ-6

------------ ፣“የአዲስ አለም ባህላዊና ታሪካዊ ጉዞ ” ጥር 26/1994 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን፣ 61ኛ አመት፣ ቁጥር 146፣ ገፅ-4

------------ ፣ “የኢራን ባህል ሳምንት” የካቲት 3/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ፣ቁጥር 153 ፣ገፅ-4

------------ ፣“ የአሳባ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ ”ሐምሌ 7/1994 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣61ኛ አመት ፣ቁጥር 307፣ ገፅ-4

------------ ፣ “የቤንሻንጉል ጉምዝ ባህላዊ ቅኝት ” (ክፍል 1) መስከረም 5/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ ገፅ-4

------------ ፣“ የቤንሻንጉል ጉምዝ ባህላዊ ቅኝት ( ክፍል 2 )” መስከረም 12/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 12 ፣ገፅ-4

----------- ፣ “የቻይና ባህላዊ ቡድን በኢትዮጵያ ትርኢቱንእንደሚያደርግ ተጠቆመ ።” መስከረም 25/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 25፣ ገፅ-1

----------- ፣ “የባህል ፖሊሲው እንዴት ይፈፀም?” ጥር 2/1995 ዓ.ም ፣አዲስ ዘመን 62ኛ አመት፣ ቁጥር 122፣ ገፅ-5

----------- ፣ “የባህል ፖሊሲው እንዴት ይፈፀም? ” ጥር 27/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 147፣ ገፅ-5

----------- ፣ “ባህላዊ ገፅታዎች በአይዳ ብሔረሰብ” ሐምሌ 15/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት ፣ቁጥር 315፣ ገፅ-5

----------- ፣ “ባህላዊ የሽክላ ጥበብ በአሊያንስ” ነሐሴ 13/1995 ዓ.ም፣ አዲስ ዘመን ፣62ኛ አመት፣ ቁጥር 343 ፣ገፅ-5

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያና አስተያየት

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከ1994 - 1995 ዓ.ም ባሉት አመቃት ውስጥ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ባህል ነክ ዜናዎችንና መጣጥፎችን በመሰብሰብ መዘርዝሮቻቸውን ከነአጫጭር መግለጫዎቻቸው ጋር ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በተጠቀሱት ዓመተ ምህረት ውስጥ አብዛኛዎቹ ባህል ነክ ፅሁፎች ዜናዎች ሲሆኑ አቅራቢዎቻቸውም የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ( ኢዜአ፤ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል (ዋኢማ) እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ ርዕሶች ከተዛማጅ ሃሳቦች ጋር ሲነሱ ይታያሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ አዘጋጆቹ ያልታወቁና በልዩ ልዩ ግለሰቦች የቀረቡ ናቸው፡፡ በተለይ በግለሰቦች የቀረቡትን የራስ አስተያየትን መስጠት ጎልቶ ይንፀባረቅባቸዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ባህል ነክ የሆኑ ውይይቶችን ፣ አለባበሶችን እና ድርጊቶችን መሰረት ያደረጉ መጣጥፎች ይገኙበታል፡፡

የፅሁፎቹ ይዘቶች በደምሳሳው ስናይ መጣጥፎች ገዢው ፓርቲ ለባህል ከፍተኛ ግምትና ትኩረት እንዲሰጥ የሚጠቁሙ ፣ የተለያዩ ጎጂ ባህሎችን ነቅለው የራሳቸውን አስተያየት የሚጠቁሙ ፣ ባህላችን እየጠፋ መሆኑን ገልፀው መፍትሄን የሚጠይቁ ፣ የተለያዩ ብሄረ ብሄረሰቦችን ባህል የሚጠቁሙና በተለያዩ ቀውዎች ስለሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ዜናዎቹ ደግሞ ወቅታዊ የሆኑ በባህል ዙሪያ የተሰጡ አስተያየቶችን ፣ የተሻሻሉ ነገሮችን ፣ የተፈፀሙ ድርጊቶችን ያሳውቃሉ፡፡

በዚህ ጥሁዊ ፅሁፍ አቅራቢ የሁለቱ አመታት ጋዜጦች ገፅ በገፅ በማገላበጥ ለተነሳበት ርዕስ ተገቢ የሆኑ 89 ያህል ባህል ነክ ፅሁፎች ሰብስቧል፡፡ በጋዜጣውም ላይ የባህል ነክ ፅሁፎች አነስተኛ መሆናቸውም በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ብዙእንዳል ተባለ እና ሊባል እንደሚገባ ፀሃፊው ያሳስባል፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች


ALA Glossary of library and information science ,Chicago, American library Association, 1983

Kent, Allen and Harold cancour, EDS, Encyclopedia of library and information science vol-1 Network, Marcel Decker, Inc, 1968

Landav ALA Thomas, ED, Encyclopedia of librarian ship 3rd Rev. ED, network Hafner publishing company, 19966.

The new Encyclopedia Britannica, 1612, 15th ED. Chicago Encyclopedia Britannica, ***1993***

መለሰ ካሣ፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ቋንቋና ትምህርት ነክ ፅሁፎች ዝርዝርና አጫጭር መግለጫ (ከ1988-1990)፣የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለትምህርት ዲማፅ፣1990

ሰለሞን አሠፋ፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የዘመን ትውስታ አምድ ላይ የወጡ ፅሁፎች ዝርዝርና አጫጭር መግለጫዎች ከመስከረም 8/1993-ሐምሌ-1996፣የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎና ስነ ፅሁፍ ክፍለትምህርት ዲማፅ፣ 1997 ዓ.ም

ፈቃደ አዘዘ፣ "የምርምር ስራ አከዋወን እንደመግቢያ"፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣አ.አ.ዩ፣ 1982 ዓ.ም

# <u>ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው</u>

1. One who writes about books, especially in regard to their author ship, date, typography edition.
2. In between when they have common behavior for instance when they have common writer, when they try to express the same thing or situation, published on the same place or when they are gathered and put as a source documents for other writers to read and support their work or papers put as a documentation or list of documents called Bibliography.
3. For a student who need to know something about person, place or thing bibliography is the starting point of his investigation, not any as a guide to what knowledge is presently available in particular published records but also as an indication of what is known, se far as published records but also as an indication of what is known, so far as published records go where no bibliography exists.
4. Annotated gives for one specific thing by short and concrete expression.
5. Anotated is just like a note but written to express the written document in detail, or to judge the content of the document. Specially on the book list, Bibliography texts or it is a note written as an introduction on the book list of libraries.
6. Bibliography anotations tend to stop short of the critical line.